# ፕሮፌሴር ጌታቸው ኀይሌ በዝነኛው ንጉሠ ነገሥት ዘርዓ ያዕቆብ እና በታዋቂው ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ ላይ የብዕር ዘመቻቸውን አውጀዋል


## በታሪኩ ውብነህ ጌታነህ

## tarikuwgetaneh@gmail.com


*በመጀመሪያ ማንነቴን ለመግለጽ እወዳለሁ፤ ታሪኩ ውብነህ ጌታነህ እባላለሁ። በዱቄና ሥራ በአንኮበር፤ ኪዳነ ምሕረት፤ በሰላ ድንጋይ ሥላሲ፤ በዶቃቂት ሚካኤል፤ በማፉድ ሚኬኤል፤ በጉር ሥላሲ፤ በደብረ ሲና መዳሕኒዓለም፡ በደብረ በርሃን ሥላሲና በምጥማቅ አማኑኤል አገልግያለሁ። ዋዚማ ለጥቂት ግዚ ተጉለት በሚገኘው በአጃና ሚካኤል ተምሪአለሁ። አቋቋም ስለአልተማርኩ የመሪጌታነት ማዕረግ የለኝም። ክህነትም የለኝም። ይህም ሆኖ ካህናቱና ሊቃዉንቱ የሚሉት ይገባኛል። ሲሳቱም አውቃለሁ። ስህተቱም ቢገባኝም ማስተካከል አልችልም ። ሊቅ ሲሳት ማረም የሚችለው ሌላ ሊቅ ነው። ይህ ከጥንት ጀምሮ ያለ የተለምዶ ሕግ ነው። ጨዋ ካህናቱኑም ሆነ ሊቃዉኑቱን አያርምም፤ በተለምዶ ሕግ ጨዋ ዝም ነው የሚለው፤ ዝምም ስለሚል ማውቅ ያለማወቁ አይታወቅም፤ ስለዚህም ነው ጨዋ ተብሎ የሚጠራው። ከላይ በተጠቀሰው አርዕስት ላይ አስፈላጊውን ትችትና አስትያየት ለምስጠት ቡቁነቲ አጠራጣሪ ነው። እላይ እንደተባለው ጥያቀው የችሎታ ጉዳይ ነው። እኒ በሁለቱ ማህል ነኝ፤ በዱቄና ስለአገለገልኩ ከጨዋ በላይ ነኝ ፤ ተንስኡ ለጸሎት ብዮ ስለምጮህ። በሥርዕቱ ገፍቼ ስለአልተማርኩ ከካህናቱና ከሊቃወንቱ ወገንም አይደለሁም። እንዴት አድርጊ ነው እኝህን ታላቅ ምሁር በውውይት ገጥሚ የምተቸው። እንዳኢጋጣሚ ሆኖ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሊ ምሁርነታቸው በዘመናዊ ትምህርት ስለሆንና ደገምም የኒም ትምህርት በመጠኑ የዘመናችንን ትምህርት [ባይመጣጠንም] ስለሆነ ያየሁትን ስህተት ለመጠቆም እችላለሁ ብዮ እገምታለሁ፤ ከዚያም አልፎ በሚስጡት አስትያየት ላይ በትኩረት ተመልከቼ ለማረም ሳይሆን ክስተት የሆነዉን ለማመልከት በቂ የሆነ ችሎታ አለኝ ብዮ እገምታለሁ።*

*ፕሮፌሴር ጌታቸው ኀይሌ በረጅም ግዜ ታሪካቸው የሚታወቁት ውዳሴን አና ዝናን በመፈለግ ነው፤ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ መምሕር ሆነው ለምን ከንቱ የሆነውን ውዳሴ እና የማያስፍልገውን ዝና ፈለጉ ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል፤ ይህ የኛ የኢትዮጵያውን ጎጂ የሆነ ባህላችን ነው፤ ፕሮፌሰሩ ወደው ሳይሆን ተገደው ነው፤ አንድ መምሕር በዕውቀቱ ብቻ ሳይሆን በተወሳሰበ መንገድ ተከቦ ታጅቦና ሰሙ ገኖ መታወቅ አለበት፤ በረጅሙ ግዜ ታሪካችን ባህላችን የሚያንጸባርቅው በጉብዝናው የታውቀ ግለስብ በአምባገንነት አስፈራርቶና ረግጦ ሲገዛና ሲያስገዛ ነው፤ ይህ ከአልሆነ ብቁ መሪ አይባልም፤ በዝና የታወቀ ገናና መሪ ያስፈልጋል፤ አገራችን የጎበዝ አገር ነች፤ በቅርቡ አንድ ጎበዝ 20 ዓመት ደክመን የሰራነውን ቢተክርስቴያን ከመተዳደሪያ ሕጋችን ውጭ በሆነ ኀይል ነጥቆ ሲወስድ እሱ ከሕግ በላይ መሆኑን አሳውቆ ነው፤ "እኛ ከሕግ በላይ ነን" ብሎ በአዳራሹ ሲንጎራደድ ካህናቱ በቅዳሴ፤ ደብተራው በዋዜማ፤ ዲያቆናቱና መዘምራኑ በጽናጽንና በከበሮ፤ ሴቱ በዕልልታ፤ ምዕመን በጭብጨባ ሲቀበለው የነበርው ስሜት የጋለ ነበር። ከጥቂቶች በስተቀር እሱን በሆንኩ ያላለ ምዕምናን አልነበረም። በዚህ ማዕበል ውስጥ ስለሕግና ሥርዓት መናገር ዘበት ነው፤ ውግዘቱና ቁጣው አይቻልም፤ ዓይንህ ለአፈር ይሁን ተብለህ ትገፈተራለህ፤ ከአቅም በላይ ነው። ቢተክርሴቲኔያችን በታሪኳ የምትታወቀው በክርስትናዋ ሳይሆን ለአምባ ገነኖች በምትስጠው አገልግሎቷ ነው። ይህ አዲስ ነገር አይደለም፤ ክርስትና ከተቀበልን ጀምሮ ያለ ነው። በረጅም ግዜ ታሪኳ ከፖለቲካ ነፃ ሆና አታውቅም። የመንግስት ለውጥ በሚሆንበት ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ ቤተክርስቲኗን በመጀመሪያ መያዝ ግዴታ ነው፤ ተባባሬ የፖለቴካ አካል ስለሆነች። እያወደሰችና እየገዘተች ተገዥውን ታስተባብራለች። ገዥውን በጸሎት ጠላቱን በፍጥነት እንድያስገዛላት በቅዳሴ ግዚ ትማለዳለች፤ መብት መጠየቅ የናት እትዮጵያ ጠላት ነው፤ ይህ በምንባብ ግዚ ዲያቆኑ የሚለው ነው፤ ሥርዕተ ቅዳሴዉና ፖለቲካውን መለየት አይቻልም። ነገሩ የጎበዝ አገር የጎበዝ ቅዳሴ ሆኖ ነው እንጂ ሐዋሪያቱ እንደዚህ ብለው አልቀደሱም።*

*የጀግኖች ጀግና እንደተባለው መሪ መሆን የሁላችንም ፍላጎት ነው፤ አገራችን የጎበዝ አገር ነች፤ ጎበዝ ከሕግ በላይ ሆኖ የሚገዛት ነች፤ ይሕም ሆኖ ስለ አገራችን ያለን አስተሳሰብ በጣም ከፍተኛ ነው፤ ከማንም የበለጥን ይመስለናል፤ የሚያስገርመው ደግሞ መብልጣችንን የሚያመለክት ምንም ነገር የለም፤ አሁን ይህ ሁሉ ስንክሳር አዚህ ለምን አስፈለገ? ቢባል የሐተታው አስፈላጊነቱ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሊ ምን በአጠፋሁ ነው እንደዚህ ዓይነት አቤቱታ የሚቀርብብኝ? ብለው ይጠይቁ ይሆናል፤ ስለዚህ መልሱ በቅድሚያ የተስጠ እንደሆነ በተረጋጋ መንፈስ መማማርና መተራረም የሚያስችል "ሁናቴ" ለመፍጠር ታስቦ ነው፤ በተጨማሪ ዉዳሴና ዝና ከላይ እንደተጠቀሰው ባሕላችን ስለሆነ ፕሮፌሰሩ ብቻቸውን አይደሉም፤ እኛ ከሳቸው እሳቸው ከኛ አንለይም፤ ልዩነቱ የሳቸው ፈር የለቀቀ እና ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ ብቻ ነው፤ ፕሮፌሰሩ በዚህ ጉዳይ ላይ የታወቁ ናቸው፤ ከሳቸው በላይ ሌላ አዋቂ ኢትዮጵያዊ የለም፤ ብቸኛውና ታዋቂው መምህር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ መባል ግዴታ ነው፤ የአለምንም ጥርጥር ከላይ የተጠቀሰውን ጸሐፊ ፕረፌሰሩ "ደግሞ 'ታሩኩ' ብሎ ጸሐፊና 'ታሪክ' አዋቂ" ብለው እንደሚሉ በመረጃ ማቀ‑ረብ ይቻላል፤ የዚህም መረጃ ደግሞ ይህንን እንደሚሉ አትጠራጠሩ። ነገር ግን ይህንን ጎጂ ባሕል ተመልከተው ከተቀበሉት ታላቅ ምህሩነት ነው።*

*እዚህ ላይ ግልጽ ለማድረግ የምፈልግው  በዚህ ጉዳይ ፕሮፌሰሩ በስምምነትና በተረጋጋ መንፈስ አቢቱታዮን ኢንዲሰሙኝ ነው፤ በላይ በተሰጠው አርዕስት ላይ የምሰጠውን አስተያየት ተመልከተው በተፈጠረው ያለመግባባት ላይ ሰፋ ያለ መግለጫ እንዲሰጡበት ነው።  ከዚህ ሊላ የታላቁን ምሁር ስም ዝቅ ለማድረግ ያለሞሆኑን መታወቅ አለበት፤  በተጨማሪ ከመጻፍ ይልቅ ማንበብን፤አስተያየት ከመስጠት በላይ መቀበልን፤ እጅግ በጣም አድርጌ ስለማምንበት አሳብ አፍላቂዎችና ጸሐፊዎችን ለማመስገን እወዳለሁ። ይህ የመጀመሪያ ጹሑፊ ስለሆነ ለማደርገው ስህተት አስቀድሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ነገር ግን እላይ በተሰጠው አርዕስት መሰረት በሁለቱ ዘርዕ ያዕቆቦች [ይቅርታ ስም "እነ" ተብሎ መባዛት ነበረበት] ላይ ያቀረቡት ትንተና እና ውይይት በመረጃ ተደግፎ የእነዚህን ሁለት ታላቅ ኤትዮጵያውያንን ታሪካዊ ሄደትን የሚያንጸባርቅ ከሆነና  ይህ ጽሑፍ  ደግሞ*

*የፕሮፌሰሩን ሥራ ለማሰነስ በመረጃ ከተረጋገጠ ፕሮፌሰሩን ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ መሆኔን እንዲታውቅልኝ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን የፕሮፌሰሩ ትንተና እና የሰጡት አስተያየት መሰረተቢስ ከሆነና ከዚህ በፊት የሰሩት ሥራዎች እንደሚመሰክሩት ውዳሲንና ዝናን ለማትረፍ ከሆነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ በጽሑፍ የሚይስፈልገውን እርማት ማድረግ ታሪካዊ ግዲታቸው ነው ብዮ አምናለሁ። እውነት አንድ ነው፤ ስለሆነም ያለምንም ፍርሐት መነገር አለበት፤ እውነት ዋነኛ የችግር መፍትሄ ነው። እዚህ ላይ ለፕሮፌሰሩ መንገር የምፈልገው ተማሪ ሆኚ የተማርኩትና ምንም ጊዚም የማይረሰኝን ትምሕርት የጊታዉና የባሪያው ታሪክ ነው፤ ባሪያው ለጊታው በየግዜው ሰዉነቱ እንድማንኛውም ሰው ነው፤ እነደሰው ሁሉ ያስባል፤ ይርበዋል፤ይጠማዋል፤ ይደከመዋል እነደሰው ሁሉ እረፍት ያስፈልገዋል፤ እንኳን ሰው ቀርቶ እንስሳትም የሰው ልጅ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ እነሱም ይፈልጋሉ እያለ ለጊታው ያጫውተው ነበር። ኬዕለታት አንድ ቀን ጊታው የባሪያው አቤቱታ ህሊናዉን ስለአስጨነቀው በነፃ አሰናበተው። እርስዎ ታላቅ ምሁርና ጊታ ነዎት፤ እኔ ደግሞ የአሽከር ልጅ ነኝ፤ በቤቲሰቢ ምህላ አለ፤ ከትውልድ ትውልድ ለአገራችን በአሽከርነት እንድናገለግል ቋሚ ትዕዛዝ ነው፤ነገር ግን ለግለሰብ አገልጋይ ሆነን አገርን ከጎዳን ዕርግማኑ ከፍ ያለ ነው። እርሶዎም የአሽከሩን ልጅ አቢቱታ በጥሞና በሕሌናዎ እንዲመለከቱት በአክብሮት እጠይቃለሁ። መልካም ንባብ።*

## *አንደኛ፡ ስለፈላስፋው ዘርዕ ያዕቆብ የተሰጠው ትርጉምና እና ትንተና*

### *"ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ በሚባል ሰም የሚታወቀው የወርቂ የሕይወት ታሪክ"*

### *ትርጉም በጊታቸው ኀይሌ*

### *ኮሌጅቬል [ሚኒሶታ] 2006*

***ፕሮፌሰር ጌታቸው ትንተናቸውን የሚጀምሩት በመዘከር ነው፤ "ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብን ከግዕዝ ወደ አማርኛ እንድትተረጉመው የገፋፋኝ አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ስለሆነ መታሰቢያው ይሁንልኝ፤" ብለው ወደራሳቸው ትንተና "መቅድም" ይገባሉ፤ ይህ ከትርጉሙ በፊት በመጀመሪያው 12 ገጾች የተጻፈው አስተያየት ነው፤ ከአስተያየቱ መጨረሻ ገጽ ላይ እንደተጻፈው ተጽፎ የተጠናቀቀው የካቲት 15 ቀን 2006 ነው [February 22, 2014]፤ አስራምስት ክፍል ያለው በግዕዝ የተጻፈው ሐተታ 32 ገጽ የያዘ ትርጉም ነው፤ እንደሚመስለኝ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ የተተረጎመ አይመስለኝም፤ ሆኖም ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ሙያቸው ትርጉም ስለሆነ ሥራው በሚገባ ተሰርታል ማለት ይቻላል፤ ችግሩ ግን አስተያየቱና ትርጉሙ ፈጽሞ አይገናኙም፤ እዚህ ላይ የሚሰጠው ትችት ፕሮፌሰሩ በዘርዕ ያዕቆብ ፍልስፍና ላይ በሰጡት አስተያየት ብቻ ይሆናል፤ አንባቢም ተሳትፎ አስትያየት እንዲሰጥበት አስተያየታቸውን በአባሪነት ይቀርባሉ፤ እዚህ ላይ አንባቢ እንዲገነዘበው የማሳሰበው ፕሮፌሰሩ የተጠቀሙት "አልፍ" "አ" ሲሆን እኔ ደግሞ "ዓይን" "ዓ" ነው፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ የቋንቋ መምሕር ሰለሆኑ ምናልባት "አልፍ" "አ" ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እኔ ፊደል በቆጠርኩበት አካባቢ ዘርዕ ያዕቆብ የሚጻፈው "በዕይን" "ዕ" ነው፤ ይህ ለትችት ሳይሆን አንባቢ እንዳይደናገር በማለትና አይነተኛ የአጻጻፍ ስልት ሊኖረን ይገባል ብሎ ለማሳሳብ ነው፤ በተለይ የቋንቋ መምሕር ግድየለሽ ሊሆን አይገባም።***

***ፕሮፌሰር ጌታቸው ትንተናቸውን የሚጀምሩት ታዋቂ ናቸው ብለው በሚያስቧቸው አውሮፓውያን ሊቃውንት ነው። ወዳጃቸው አቶ አሰፋ ገበረ ማርያም ፕሮፌሰሩን የጠየቁትና የገፋፉት በግዕዝ ዘርዕ ያቆብ የጻፈውን ፍልስፍና ወደ አማርኛ እንዲተረጉሙትና እኛ ኢትዮጵያውያኖች የራሳችን ፈላስፋ የሚለዉን አንብበን እንድንረዳ ነበር። አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ከዚህ ውጭ ሊላ ነገር የሚፈልጉ አይመስልም። የጠየቁት እንዲተረጎምላቸው ነው። ለዚህም ነው "መታሰቢያው ይሁንልኝ" ያሉት። ቃል በገቡት መሰረት በቀጥታ "ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብን ከግዕዝ ወደአማርኛ" ተርጉመው ለወዳጃቸው መታሰቤያ ቢያበረክቱ ኖሮ እዚህ ውይይት ከመግባት ይልቅ አማርኛውን እያነበብን ፍልስፍና ምን እንደሆነ እንማረበት ነበር። ነገር ግን ከዘርዕ ያቆዕብ ፍልስፍና አስቀድመው የራሳቸውን ትንታኔ በአውሮፓውያን ሊቃውንት አጅበው አቀረቡ። እዚህ ላይ አንባቢ በትኩረት መመልከት ያለበት ፕርፈሰሩ በቅድሚያ አሳባቸውን መስጠት የለባቸውም ማለት አይደለም፤ በአግባቡ ሊሰጡ ይችላሉ፤ አግባብ ማለት ሥርዓት ማለት ነው። በ 12 ገጾች ላይ የተጻፈው መቅድም ከሥርዓት ውጭ ነው። ፕሮፌሰሩ ራሳቸውን ከማንኛውም ሥርዓት በላይ [ከሕግ በላይ ነኝ እንዳለው ጎበዝ ማለት ነው] ነኝ ስለሚሉ ይህንን አስትያየት አይቀብሉም፤ እሳቸው ተቀበሉት አልተቀበሉት ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም። ነገር ግን ለአንባቢ ሥርዓት አልባ መሆን ሕብረተሰብን አጥፊ መሆኑን ለመጠቆም ነው። አገራችን የጠፋችው ከሕግ በላይ ነን በሚሉ አምባገነኖች ነው፤ ፕሮፌሰሩ ምገደኛ አምባ ገነን መሆናቸዉን አያውቁትም፤ ይህ የአምባ ገነኖች ባሕርይ ነው። በሥነ ጹሕፍ ደንበ ሥርዓቱ እንዲት እንደተጣሰ በዝርዝር አስረዳለሁ።***

*አንደኛ፡ በመጽሐፉ አርዕስት መሰረት ስምም ጸሐፊም አሉት፤ ጸሐፊው የመጻሐፉ ባለቤት ነው፤ አርዕስቱ ፍልስፍና ነው። እንግዲህ ዘርዕ ያዕቆብ ባለቤት ሲሆን "ሐተታ" የተባለው ደግሞ አርዕስት ይሆናል ማለት ነው። በሥነ ጽሑፍ ሥርዓት መሰረት ባለቤት በተቀዳሚነት ይቀርባል፤ አቀራረቡ ቅደም ተከተሉን ከተከተለ ትንታኒዉን አቅራቢ በመሰለው መንገድ ስለባልቤቱ ሊያቀርብ ይችላል፤ በመጀመሪያ ደርጃ ባለቤቱን ማስተዋወቅ አለበት፤ ትምህርቱን ሙያዉን ሥራውን አጠር በአለ መልኩ ለአንባቢ ማስተዋወቅ ግዴታ ነው፤ ከዚህ በመቀጠል በተሰጠው አርዕስት ላይ ለመጻፍ ምን እንዳነሳሳው አጠር ያለ መግለጫ መስጠት አስፈላጊ ነው። ለዚህም መረጃ የሚሆን ከመጻሐፉ ላይ ቀንጠብ አድርጎ ማቅረብ ለሚሰጠው ትንተና ግልጽና ተጨባጭ የሆነ መረጃ ይሆናል፤ ለምሳሌ መጽሐፉን ለመጻፍ ምን እንዳስገደደው መጥቀስ አስፈላጊ ነው።*

*ሁለተኛ፡ ስለአርዕስቱ ሰፋ ያለ መግለጫ መስጠት ግዴታ ነው፤ አንባቢው ትምህርት ማግኘት የሚችለው አርዕስቱ ምን እንደሆነ ሲገባው ነው፤ ይህ ከአልሆነ ለማንበብ ፍላጎት አይኖረውም፤ ስለዚህ ፍልስፍና ምን እንደሆነ ቃል በቃልም ሆነ በምሳሊ ማስረዳት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፤ ለምሳሌ ፍልስፍና ማለት የሥነ ፍጥረትን ሁኒታ በአንክሮ መመልከት ነው ማለት ይቻላል፤ ግን ይህ በቂ ሊሆን አይችልም፤ የፍልስፍና ታሪካዊ ሄደት በሚገባ መቅረብ አለበት።*

*ሶወስተኛ፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት ወይም ትችት ከአለ በአጭሩ ከመረጃ ጋር ማቅረብ ለአንባቢው የበለጠ ትምህርት ይሰጣል፤ የራሱኑም አስተያየት እንዲሰጥ ይገፋፋዋል፤ በተጨማሪ ሃሳብ በነ ፃነት ሲንሸራሸር መላምቱ ይዳብራል፤ ውጢቱም የተሳካ ይሆናል። በፍልስፍና ላይ የሚደረግ ውይይት ማለቂያ የለውም፤በየምክናያቱ ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ፤ ፍልስፍና "ሁኔታን" ለዋጭ ኀይሎችን በትኩረት ይመለከታል፤የወጣ ይወርዳል፤ የወረደ ደግሞ ተመልሶ ይወጣል፤ ይህ ፉጡራዊ ሕግ ነው፤ የዚህን ፉጡራዊ ሕግ ፈላስፉ ይመረምራል፤ የመመርመሪያውም የራሱ የሆነ ልዩ ዘዴ አለው፤ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱተን የሥነ ጽሑፍ መምርያ መሰረት በአጭሩ ስለ ፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ። ይህ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ጽሑፍ ታሪካዊ ሄደት ነው፤ ይህም ሆኖ ለተለያዩ ትምህርት የየራሱ ዘይቤ አባባልና ቋንቋ ፤ ቃላት አገባብና ዓረፍተ ነገር አሰካክ አለው፤ የግስ እርባታዎች፤ መስተዋድድና መስተፃምር፤ ገቢርና ተግብሮ፤ በሳቢና ቤተሳቢ ዘርፍ በትክክል ሕጋቸውን ማንፀባረቅ አለባቸው። በፍልስፍና ላይ ዝርክርክ የሆነ ዕረፍተ ነገርና ደረጃውን ያልጠበቀ ቃላት አይጻፍም። የአጻጻፉን ምሳሌ እንመለከት።*

*ዘርዓ ያዕቆብ የብዕር ስሙ ነው። እርሱ ግን የክርስትና ስሜ ነው በሎ ጽፏል፤ ደግሞ የመጠሪያ ስሜ ወርቄ ነው ይላል፤ ነገር ግን ፍልስፍናዉን የጻፈው መጽሐፍ "ሐተታ ዘዘርዓ ያዕቆብ" በሚል አርዕስት ነው። የትውልድ አገሩም አክሱም ነው ይላል፤ አክሱምም በሚኖርበትም ግዚ የሚታወቀው በወርቄ ነው ይላል። እዚህ ላይ አንባቢ በቱከረት መመልከት ያለበት የዚህ ፍልስፍና መጽሐፍ ጸሐፊ በውነተኛ ስሙ መጠራት ያለመፈለጉን ነው። ለምንድነው በስሙ መታወቅ ያልፈለገው? ይህ ይህንን መጽሐፍ እንመረምራልን የሚሉ ጸሐፊዎች ስራ ነው። ይህ ከተባለ በኋላ ምክናያቱን መፈለግ ነው። በመጽሐፉ ላይ የተጻፈው ስለሚያስጠየቅዉና ስለሚያስከስሰው በብዕር ስም ተደብቆ ስለመጽፉ ምንም ጥርጣሪ የለም፤ የትም አገር ተሂዶ ቢፈለግ ወርቄ የሚባል ሰው አይገኝም፤ ይህ መላ ምት ነው፤ ማለትም ሊሆን ይችላል ተብሎ ነው፤ላይሆንም ይችላል፤ ነገርግን በዚህ ላይ ሃሳብ ቢንሸራሸር ከዚህ የተሻለ መላ ምት ሊመጣ ይችላል። እዚህ ላይ በፍልስፍና ሙያ የተሰማሩ ሊቃውንት በአንድነት የሚስማሙት ነገር ቢኖር ዘርዕዓ ያዕቆብ በብዕር ስም ተደብቆ የጻፈበት በቂ የሆነ ምክንያት አለ፡ እሱም "<u>ሁኔታ</u>" ይባላል። ዓለማዊና መንፈሳዊ በመጽሐፍ ላይ በአንድነት ሆነው ተተንትነው ሊጻፉ "ሁኔታው" አይፈቅድም። መጽሐፉ እንደተገኘ ሃይማኖተ ቢስ ተብሎ ተውግዟል፤ ጸሐፊውም ቢገኝ ኖሮ በመቋሚያ ተደብድቦ ይገደል ነበር። ይህ ስለ ዘርዕ ያዕቆብ ማንነት የተሰጠ አጭር መግለጫ ነው። ስለትምህርቱና ሙያው አርዕስቱ ላይ በሚደረገው ውይይት በአጭሩ ይጠቀሳል።*

*ስለ አርዕስቱ ሰፋ ያለ መግለጫ መስጠት አስፈላጊ ነበር፤ ነገር ግን ይህ በአጭሩ የተጻፈ አስተያየት ስለሆነ በዝርዝር ስለፍልስፍና ታሪካዊ ሄደት ማቅረብ አስቸጋሪ ነው፤ ስራው ብዙ ነው፤ ከላይ እነደተጠቀሰው ፍልስፍና ማለት የሥነ ፍጥረትንና የሕብረተሰቡን "ሁኔታ" መመርመር ማለት ነው፤ እጅግ በጣም ሰፊ ስለሆነ ፍጡራዊና ሰው ሸራሽ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ትኩረት በተሞላበት ዘዴ ይመረምራል፤ ተመራምሮ ዉጢቱን ለሕብረተሰቡ ያሳውቃል፤ ያስተምራል፤ የወደፊቱን "ሁኔታ" በትንቢት ሳይሆን በምርምር ጠንቅቆ ያውቃል፤ "ሁኔታዎች" እንዴት እንደሚከሰቱና እንዴት መለወጥ እንደሚችሉ ጠንቅቆ ያውቃል። ዘርዕዓ ያዕቆብ ጹሑፉ ላይ እንደሚታየው በታላቅ ደረጃ የተማረ ሊቅ ነው፤ ዳዊት አንብቧል፤ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን በሚገባ ያውቃል፤ ሙያው ማስተማር መሆኑን አያጠራጥርም፤ ጽሑፉኑም የጻፈው በሚያስተምርበት ወቅት ነው፤ ዋሻ የተባለው እንደስሙ መደበቂያ እንጂ የጽሑፉ መጻፊያ ስፍራ አልነበረም፤ የኢትዮጵያ ታላላቅ መጻሕፍት የተጽፉት በገዳም ውስጥ ነው እንጂ በዋሻ አይደለም፤ ብራናው ተፍቆ ብዕሩ ተቀርፆ ቀለሙ ከተለያዩ ንጥረ ነገሮች ተበጥብጠው የሚሰሩት በትምህርት ቤት አካባቢ ነው፤ ዋሻ ውስጥ ተደብቆ እነዚህን ሁሉ አቀነባብሮ በሁለት ዓመት ውስጥ የፍልስፍና መጽሐፍ ጻፈ ማለት ያስቸግራል፤ በአጭሩ ፍልስፍና ዋሻ ውስጥ ተደብቆ በጾም በጸሎት የሚመጣ ነገር አይደለም፤ ከሕብረተሰቡ ጋር ሆኖ "ሁኔታዉን "በትኩረት ማጥናት ግዴታ ነው። ዘርዕዓ ያዕቆብ ምናልባት ትውልደ ቤተ እስራኢል*

*ሳይሆን አይቀርም የማለት ግምት አለኝ፤ በውይይቱ ላይ ሃይማኖትን አጥብቆ የዚህ ወገን ወይም የዚያን ወገን አይልም፤ እምነት አንድ ነው አንዱ ከሊላው አይበልጥም ይላል፤ ፈጣሪዉንም ይጠይቃል፤ ለምንድ ነው ላንዱ ተገልጦ ለሌላው የማይገለጠው ብሎ ከራሱ ጋር ይወያያል፤ ችግሮች የሚፈቱት በውይይት ነው፤ፍልስፍና ማለት ይህ ነው። ሐተታዎቹ ብዙ ስለሆኑ አንባቢ ግዜ ወስዶ ሙሉ መጽሐፉን ማንበብ ይኖርበታል። ሐተታ ስለተባለው በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት አስተያየቶች ጋር በአጭሩ እንወያያለን።*

*በሶወስተኛ ደረጃ ስለ " ሐተታ ዘዘርአ ያዕቅብ" በሚሰጠው አስተያየት ላይ ስለ መጻሐፉ ቀደም ብሎ የተሰጠ ትችት ከአለ እንደአስፈላጊነቱ በአባሪ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ይህም ሲባል ጸሐፊ መጽሐፉን ስለተቸ ብቻ በውዋቤነት መቅረብ የለበትም ትችቱ በበቂ መረጃ ታግዞና ደረጃውን ጠብቆ የተጻፈ ጽሑፍ መሆን አለበት። ነገር ግን በቅድሚያ "ሐተታ" ስለተባለው በቅጡ መዋያየት አስፈላጊ ነው። ቡዙዎቻችን ስለ ዘርዕ ያዕቅብ የሰማነው ክላውድ ሳምነር የሚባሉ በአዲስ አበባ ዩነቨርስቲ የፍልስፍና ፕሮፌሰር በአሳታሙት መጽሐፍት ላይ ነው፤ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ፍልስፍና በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ የዘርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት Treatise በሚል አርዕስት በ 1994 [ኢ. ኢ.]የታተመ መጽሕፍ ነው፤ ፕሮፌሰሩ በእንግሊዘኛ የተጻፈውን "treatise" የሚለውን "ሐተታ" ብለው ተርጉመዉታል፤ መምሕሩ ከአምሳ ዓመት በላይ በዩነቨርስቲው ስለቆዩ ምናልባት "ሐተታ" ያሉት ትርጉም በፍልስፍና ዓለም ውስጥ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ በጉባኤ "ሐተታ" ማለት የፍልስፍናን ውውይት ውጢት ያንጻባርቃል ተብሎ ተደንግጎ ሊሆንም ይችላል፤ነገር ግን በእርግጠኛነት ሆኜ እዚህ የሐተታን ትርጉም ልጽፍ አልችልም፤ ግን ከአንባቢ ጋር መወያየት የሚያስፈልገው "ሐተታ" የተባለው ቃል አመጣጡንና ይዘቱን ነው፤ አመጣጡ ሐተተ ከሚለው ግሥ ነው፤ ይዘቱ ደግሞ በተለምዶ አማርኛ "ሐተተ" ማለት ነገር አበዛ ይሆንና "ሐተታትህን አታብዛ" ይባላል፤ ይህም ማለት አጠር አድርገህ አስረዳ ማለት ስለሆነ "Treatise" ለተባለው ቃል ትክክለኛ መግለጫ ሊሆን አይችልም፤ ሆኖም ሊቃውንቱ ተወያይተው በስምምነት ይሁን ከተባለ ሕግ ስለሆነ መከበር አለበት። በዚህ ሙያ የተሰማሩ መምሕራን በዚህ ጉዳይ ላይ እስካሁን ድረስ የሰጡት መግለጫ ስለሌለ ሃሳብ እንዲሸራሸርበት ለየት በአለ ቃል ይቀርባል። ለግዚው "Treatise" የተባለውን ቃል "ንጥረ ነገር" ብለን መተርጎም ግዴታ ይሆናል፤ ይህም ማለት ሃሳቦች በውይይት ተንሸራሸረው በመጨረሻ በስምምነት የተገኘ ነገር ማለት ነው፤ ሆኖም እንደዚህ አይነት አገላለጽ በአንድ ግለሰብ የሚወሰን አይደለም፤ መወሰን ያለበት በጉባኤ መሆን አለበት፤ ያ ጉባኤ ደግሞ የሜሰየመው በሊቃውንቱ ነው፤ ባሁኑ ግዜ ኢትዮጵያ እንኳንስ ሊቃውንት ቀርቶ የሊቃውንት ደቀ መዛሙርት የላትም፤ ከፍ ያለ የአገር ውድቀት ነው፤ ሊቃውንት የሚያስገኝ "ሁኔታ "እስኪፈጠር ድረስ "ንጥረ ነገር" የተባለውን ለግዜው ተቀብሎ መወያየቱ አይከፋም። ከእንግዲህ ወዲህ ውይይቱ የሚቀጥለው "ንጥረ ነገር" እየተባለ ይሆናል።*

*ይህንን ግዜያውዊ "ንጥረ ነገር" ተብሎ የተተረጎመውን ቃል ትርጉሙን ማስረዳት አስፈላጊ ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙ እንዲህ ሊሆን ይችላል፤ ፈላስፋው አንድ ነገርን መርምሮ አንጥሮ አጥሎና አስተካክሎ በጽሑፍ ሲያቀርብና ሌሎች ፈላስፋዎች ይህንን ግኝት አጥንተውና መርምረው እውነት ነው ብለው ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ግኝቱ በእርግጥ ራሱን የቻለ ፍልስፍስፍና ይሆናል። ይህም ሆኖ ፈላስፋ ሁሉ "በንጥረ ነገር" የተደገፈ አዲስ ነገር ይፈልስፋል ማለት አይደለም፤ በዓለም ሁሉ ከአሉት ፈላስፋዎች በንጥረ ነገር የተደገፈ ፍልስፍና ያገኙ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ፈላስፋዎች ሁሉ ያለሟቋረጥ ይመራመራሉ፤ ሥነ ፍጥረትን የማይመራመር ፈላስፋ አይባልም፤ ዘርዕ ያዕቆብ ሥነ ፍጥረትን የተመራመረ ፈላስፋ ነው። ነገር ግን ፕሮፌሰር ሳምነር እንደሚሉት "በንጥረ ነገር" የተደገፈ ምንም ዓይነት አዲስ ግኝት የለውም፤ ውይይቱ ሁሉ አለማዊና መንፈሳዊ ሆኖ በውስጣቸው ያለውን ቅራኔ ለመቅረፍ በሚገባ ተወያይቷል፤ ለፈጣሪው አግባብ ያላቸውን ጥያቂ አቅርቧል፤ የተለያዩ እምነት ተከታዮችን ተችቷል፤ ስለንብ ሥራ ሲፈላሰፍ እንዲህ ይላል፤ "ንቢቱ የተለያዩ አበባዎችን ትቀስማለች፤ በዚህም ምክናያት ጣዕም የሚሰጥ መዓዛው የሚጣፍጥ ማር ትሰራለች፤ ማርም ለሰው ልጅ እርካታ የሚሰጥ መጠጥ ይሆናል፤ በተጨማሪ ለጨለማው ብርሃን የሚሰጥ ጧፍም ይሆናል፤ የሰውም ልጅም አንድንዷ ከተለያዩ ሁኔታዎች ቢቀስም ዕውቀትን ያገኝ ነበር ይላል [ከላይ የተጠቀሰው ከመጻሕፉ ላይ ሳይሆን በአእምሮዮ ያስታወሰኩትን ነው]፤ ስለ ሥነ ፍጥረት ሲፈላሰፍ ደግሞ "ፍጥረት ያለ "ፈጣሪ" ሊኖር አይችልም" ይላል።*

*በተጨማሪ ፈላስፋው በክፍል አንድ ላይ ስለትውልደ አገሩ በአጭሩ አስረድቶአል፤ ነገር ግን ከአጻጻፉ ላይ አንባቢ በአትኩረት መመልከት ያለበት "የቅዱሳተ መሳሕፍትን ትርጓሜ ለመማር" ከአገሬ ርቄ በመሄድ በአገራችንና በውጭ መምሕራን "ትርጓሜን ተማርኩ" የሜለውን መነሻ ነው፤ መድረሻው ደግሞ የሁለቱንም የመጽሐፍ ትርጓሚ ሕሌናዮ አልቀበል ስለአለ "ዝም አልኩ"ያለውን ነው፤  በዚህ መነሻና መድረሻ ረገድ ዘርዕ ያዕቆብ ከሁለቱም የተለየ ነፃ የሆነ ሕሌናውነት አዳብሮ መመራመር ጀመረ ማለት ነው። ዝም ያለበትም ምክናያት በነፃነት ማሰብ የማይቻልበት "ሁኔታ" ስለሆነ ነው፤ ለዚህም ከጽሑፉ በላይ የሚቀርብ መረጃ አይኖርም። በክፍል ሁለት ላይ ዘርዓ ያዕቆብ የሚያሳየን በግዜው የነበረውን ከፋትና ጭካኔ፤ ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚያደርገውን በደል ነው፤ ለዚህም መረጃ የሚሆነው የሚኖርበትን ዋሻ እንደመንግስተ ሰማያት አድርጎ*

*መመልከቱ ነው፤ ይህም የሚያሳየው ሰው ምን ያህል ከፉ እንደሆነ ነው። እዚህ ላይ ተመራማሪ ፈላሰፋ በትኩረት ማየት ያለበት በዘርዓ ያቆብ ግዜ የነበረውን "ሁኒታንና" የአሁኑን ነው። እንግዲህ የዘርዓ ያዕቅብን ፍልሰፍና የምናየው ከሥነ ጹሑፍ ሄደትና ከሕብረተሰቡ ታሪካዌ ሄደት ጋር ይሆናል። ፍልሰፍና ሕብረተሰብና ሥነ ጹሑፍ አንድ ናቸው፤ ለነዚህ አንድነት "ሁኔታ" ከአልተፈጠረ ሕበረተሰቡ ታሪካዊ ሄደት አይኖረውም። እንደዚሁ መንሰዋለል ይሆናል፤ ፍልሰፍናም ታሪከም ሥነ ጽሑፉም አይኖረዉም፤ እረኛው እንደጠፋበት በግ ይበታተናል፤ አቅጣጫዉንም የሚሆነውንና የማይሆነዉን ለይቶ ሊያውቅ አይችልም፤ ወደተፈለገበት የሚነዳ የሚዳ "አሕያ" ሆኖ ይቀራል።ይህም ስለሆነ ግብዞችና የበላይ ነን የሚሉ አካል አሸከሮች ለሰው ልጅ የሚሰጠዉን ክብር ነሰትው "አሕያ" እንደሚሉት ነው።ዘርዕ ያቆብ በሥነ ጽሑፉ ላይ ትቶሉን ያለፈው ፍልሰፍና የሚያሳየው በግዜው የነበረዉን "ሁኒታ" ነው። በጽሑፉም እያንዳንዱ ቃል የሚያንጸባርቁት ሕብረተሰቡን ያለብትን "ሁኔታና" ሕሊናዊነት ነው፤ ይህም ማለት በተወሰነ ሰፍራና ግዜ ሁኒታው አሰገድዶ የሕበረተሰቡ ሕሊናዊነት በጽሑፍ ሰፍሯል ማለት ነው፤ ጽሑፉም የሚያመለከተው በላይ በተጠቀሱት መላምቶች ተቀነባብሮ በአጋጣሚ ሳይሆን በታሪካዊ ሄደት የተገኘ ዉጤት ነው፤ የዘርዕ ያዕቅብም ፍልሰፍና ዉጤት በታቀደው መሰረት የሰው ልጅ ለሚያደርገው ተግባር ሁሉ ሥርዓት እንዲኖረውና የተፈጥሮ ሕግን እንዲከተል ነበር።*

*ነገር ግን ፈላሰፋው በጽሑፉ ላይ እንዳለው በዘመኑ በተረጋጋ መንፈስ ፍጥረትን መመራመር ስለማይቻል በብዕር ስም ተደብቆ የፉጡራዊ ታሪካዊ ሄደትን ለማካፈል ጥረት አድርጓል። እንጊዲህ አንባቢ በትኩረት መመልከት ያለበት በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንት የዘርዓ ያዕቆብን ሥነጹሑፍ ተመልከተው ቢወያዩበት ኖሮ የሕብረተሰቡ ታሪካዌ ሂደት የት ይደርስ ነበር? ብሎ መመራመሩ አግባብ ነው ብዮ አሰባለሁ። ነገር ግን የዘርዕዓ ያዕቆብ ሥነ ጽሑፍ እንደ ሃይማኖተ ቢስ ስለተቆጠረ ተወገዘ፤ የሥነ ጽሑፍም ታሪካዊዌ ሂደት በአለበት ቆመ፤ ለዚህም መረጃ የሚሆነው የሕብረተሰባችን ያለብተን "ሁኔታ" ነው፤ ሥነ ጽሑፍ አልባ መሆን እርግማን ነው፤ በአለፈው አንድ መቶ ዓመት ውሰጥ ሥነ ጽሑፍ ተብሎ ሊጠቀሱ የሚችሉ ከሶወሰት ወይም አራት አይብልጡም፤ ሕሩይ ወልደሥላሴ [የሥነ ጽሑፍ ሊቅ]፤ ከበደ ሚካኢል [የሰንኝ ሊቅ] ሐዲስ ዓለማየሁ [ የሕብረተሰብ ሁኔታ የልብ ወለድ ሊቅ] ዳኛቸው ወርቁ [የሕብረተሰባዊ ሕሊናዌነት ትንተና ሊቅ]። ሆኖም ሥነ ጽሑፍ በሕብረተሰባችን ስለአልዳበረ የማንበብ ልማድ አልተለመድም፤ ከላይ ከተጠቀሱት በላይ አለ የሚባል ሥነ ጽሑፍ የለም፤ ከአለም ሕሌናውነታችንን የሚያዳብር ሳይሆን እንደገድል ማሚቶ የሌላ ሕብረተሰቦችን ታሪካዊ ሄደት የሚያስተጋባ ነው። ሥነጽሑፍ የአንድ ሕብረተሰበን ታሪካዊ ሄደት ከትውልድ ትውልድ የተላለፈውን ቅርስ በሥነ ጽሑፍ ዳብሮ ሲጻፍ ነው፤ ይህም ማለት የቃላት አገባብና የዕረፈት ነገር አሰካከ፤ የጽሑፉን ጥራትና ይዘት ጽንሰ ኀሳቡን የሕብረተሰቡን አጠቃላይ "ሁኔታ" አንጸባርቆ በከፍተኛ ደረጃ ተቀነባብሮ ሲቀርብ ነው። እንዲህ ያለው "ሁኔታ" እንዳይፈጠር በዘርዓ ያዕቅብ ፍልሰፍና ላይ የተሰጠው አሰተያየትና ትንታኔ እንደመረጃ በአጭሩ ለአንባቢ ይቀርባል።*

*በመጀመሪያ ባጭሩ ስለፍልሰፍና ታሪክ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ፈላሰፋ ሲመራመርና ሲፈላሰፍ የአለምንም ፍርሃትና የሕሌና ሸብር መሆን አለበት፤ ለዝና እና ለዉዳሲ ከሆነ ግን ፍልሰፍና አይሆንም፤ ምክንያቱም ፍልሰፍናው በመሰረቱ ዉዳሴና ውግዘት ስለሚሆን በተጨባጭ ያለዉን "ሁኔታ" አያመለከትም፤ለምሳሌ በአገራችን በሚያሰፈራ "ሁኔታ" የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ነን ብለው በማስተማር ላይ የተስተማሩት ወንጌላዉያን ነን የሚሉ ፍልሰፍና ዉስጥ ገብተው የሕብረተሰቡን "ሁኔታ" ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናኘት የጥንቆላ ስራ ሲሰሩበት በግልጽ ይታያል። የሰው ልጅ ክብሩ ተገፎ ዘሩ እንዲጠፉ ባአለበት "ሁኔታ" ላይ ተብዳዩን ተበድያለሁ ስለአለ ብቻ ያወግዙቷል፤ እንደ ቢተክርሲቲያንም ጠላት ተደርጎ የሚታየበትም ሁኔታ ተፈጥሮአል፤ ይህ በጉልህ የሚያሳየው ሕብረተሰቡ በምን ዓይነት "ሁኔታ"ላይ እንዳለ ነው፤ ለምሳሌ በግሪክ ሕብረተሰብ ውስጥ ሶክራትስ የሜባል ፈላሰፋ "ከግሪክ ዉጭ የመጣ ጣዖትን ታመልካለህ" ተብሎ በግሪክ ሕብረተ ሰብ ስለተወገዘ በሞት እንዴቀጣ ተፈርዶበታል፤ በዚህም ምክንያት ሊዮንና ፐላቶ የተባሉ ፈላሰፋዎች "በግሪክ አስተዳደር ስርዓት ዉስጥ ሕሌናዉነቱ የዳበረ ሰው ሊኖር አይችልም " ሲሉ ምስክርነታቸዉን ሰጥተዋል። በአንፃሩ ደግሞ በማግና ካርታ [1215 ዓ.ዓ] ድንጋጌ መሰረት ንጉሡ ምንም እንኳ ንጉሥ ቤሆን ከሕግ በላይ መሆን የለብትም ስለተባለ የሰው ልጅ የሕግ ተገዥ እንዲሆን አስትዋፃኦ አድርጓል። ቀደምም ሲል የተጻፉ ጽሑፎች የሥነ ጽሑፍን ታሪካዊ ሄደት በሚገባ ያመለከታሉ፤ የሆመር ኢሊያድና ኦዲሲ ለግሪክ ሕብረተሰብ ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያው ነው፤ ከጊታ ልደት በፊት አንድ ሺህ አንድ መቶ ዓመተ ዓለም የነበረው ሆመር በዝና የሚታወቀው በቅኔ አና በማኅሌት ነበር፤ጽሑፉም መወድሰና ዜና መዋዕል ስለነበሩ የሚያንጸባርቁት አምስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ነው። ይህም ሆኖ የሆመር ጹሑፍ የግርኪን ሕሊናውነትን አያመለከትም፤ ሆመር ከባቤሎንያ ወደግሪክ የተሰደደ ስለሆነ የሚያንጸባርቀው የመጣበትን ሕብረተሰብ ነው፤ ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ምሳሌ ፈልሰፋ ገደብ በሊለው ነፃነት ሲመራመርና ግኝቱን ለሕብረተሰቡ ሲያካፍል ሕልናዌነት ይዳብራል፤ መጥፎ ሁ"ኔታዎች" ወደ ጥሩ "ሁኒታ" ይለወጣሉ፤ እንግዲህ ይህ ከተባለ በኀላ ውይይታችን በተረጋጋ መንፈስና ደረጃውን በጠበቀ መከባበር ይሆናል።*

*ስለ ዘርዓ ያዕቆብ የተደረገው ውይይት ስለ "ፍልሰፍናው" መሆኑ ቀርቶ መጽሐፉን ማን እንደጻፈው መሆኑ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው። የፐሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ዋና ትኩረት ይህ ነው። ከሳቸው አስተያየት በፊት ግን በሙያ ፍልሰፍናን ያጠኑ*

*መምህራን የሰጡትን አስተያየት በአጭሩ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፤ እነዚህ የኢትዮጵያ ፈላስፋዎች ራሳቸው በግዕዝ የተጻፈዉን መጽሐፍ ፈልገዉና መርምረው ሳይሆን ፕሮፌሰር ሳምነር ተርጉመው "የጥንታዊ ፍልስፍና ታሪክ" ተብሎ በታተመው መጽሐፍ ላይ የአደረጉቱን ርብርቦሽ ነው። ፈላስፋዎቹም ዶክተር ቀልቢሳ ወርቅነህ፤ ዶክተር አምባዮ ወንዲፍራው፤ ዶክተር መሳይ ከበደ እና ሊሎቹም ስለ ዘርዓ ያዕቆብ ሰፋ ያለ አስተያየታቸዉን ሰጥተዉበታል። እነዚህ መምህራን ምንም እንኳ ኢትዮጵያዉያን ቢሆኑ ዘርዓ ያዕቆብን የተመለከቱት በአውሮፓዉያን ዓይን ነው። የመምህራኑ አስተሳሰብ ባጭሩ የተመሰረተው በዘርዓ ያዕቆብ ችሎታና ፍልስፍና በተባለው ዝክረ ነገር ላይ ነው። የፈላስፋዎቹ መጀመሪያ ጥያቄ ፕሮፌሰር ሳምነር በምን ዓይነት መለኪያ ነው ዘርዓ ያዕቆብን ከፈረንሳዩ ፈላስፋ ደስካርትስ ጋር ማወዳደር የቻሉት? ደስካርትስ አውሮፓዉያን ስለሆነ በአስተሳሰብም ሆነ በፍልስፍና ከዘርዓ ያዕቆብ ጋር ሊወዳደር አይችልም ። የአውሮፓዉያን ርዕየተ ዓለም ከኢትዮጵያን ጋር የተለየ ከመሆኑም በላይ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ብዙ ስለተራመዱ በእነሱ ደረጃ ያለ ዕውቀት ሴኖረው አይችልም ብለው በማሰብ ነው ። ዶክተር መሳይ ከበደ "የዘርዓ ያዕቆብ አስተሳሰብ መንፈሳዌ ስለሆን እንደ ደስካርትስ ዓለማዌ ሆኖ ሴያስብ አይችልም፤" ከዚህም በላይ ደግሞ "የአውሮፓውያን ሕሊና ንቃት ከኢትዮጵያውያን ሕሊና ንቃት ጋር ሊወዳደር አይችልም፤" ማለትም በፍልስፍና ደረጃ አንድ ስለአልሆኑ ይላሉ። በዚሁ መስመር ላይ አንድ በመሆን ዶክተር አምባዮ ወንዲፍራው "የደስካርትስ ፍልስፍና ለዘርዕዓ ያዕቆብ እንግዳ ነገር ስለሆነ እንደሱ ፈላስፋ ነው ማለት ዘበት ነው፤ ፈጽሞ ዘርዓ ያዕቅብ ደስካርትን ሊሆን አይችልም" በማለት ይደመድማሉ። እዚህ ላይ ፈላስፋዎቹ በትኩረት የተመለከቱት የአውሮፓውያንን ሳይንስና ቴክኖሎጂን ታሪካዌ ሄደት ነው። ነገር ግን ደስካርትና ዘርዓ ያዕቆብ ተመሳሳይ የሆነ የሥነ ፍጥረት አመለካከት አላቸው፤ደስካርት የሰው ልጅ ሁለት ፍጥረት አለው ብሎ ያምናል፤ አንድኛው ፍጥረት እግዚአብሒር በአምሳሉ የፈጠረው አካል ነው፤ ሁለትኛው ፍጥረት ደግሞ በስተንፋሹ እፍ ብሎ የፈጠረው ነፍስ ነው ይላል። ዘርዕ ያዕቅብ ደግሞ ፍጡር ያለ ፈጣሪ አይኖርም ይላል። ይህንን ያሉት በአንድ አካባቢ ዘመን ነው። አንዱ ከአንዱ ቀዳው እንዳይባል አንዱ ኢትዮጵያ ሊላው ደግሞ ፈረንሳይ ነው ያለው። ሁለቱም መንፈሳዌና ዓለማዌ ፈላስፋ መሆናቸውን አያጠራጥርም። ፍልስፍና አንድ የተወሰነ አገር የለውም። ሼክ አንታ ዲዮፕ የሚባል የአፍርቃ ሊቅ ስለፍልስፍና ሲጽፍ እንዲህ ይላል፤ "ፍልስፍና ማለት ማንነቱንና ሲያውቅና እውነትን እውነት ከአልሆኑ ነገሮች መለየት ሲችል ነው" ይላል። ግሩም አባባል ነው። ይህም ሆኖ የኛ ፈላስፋዎች ፍልስፍናው ጠፍቷቸው ሳይሆን ትኩረት የሰጡት ሳይንስና ቴክኖሎጂው ስለሆነ ብቻ ነው። ሆኖም ዘርዓ ያቆብና ደስካርት በንጥረ ነገር የተደገፈ ያገኙት ፍልስፍና የለም። ነገር ግን ሥነ ፍጥረትን በሚገባ የመረመሩ ፈላስፋዎች ናቸው።*

*ወደ ፕሮፌሲር ጌታቸው ኀይሌ ትንተና ከመግባታችን በፊት የፍልስፍና ዕውቀትን ምዕራብውያን እንዴት አድርገው ለሁለት ከፍለው እንደሚያዉት በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ነው። አንባቢ እነዚህን ሁለት ክፍሎች በትኩረት ከመረመረ በፍልስፍና ላይ የሚደረገውን ውይይት ለመከታተል ይረደዋል ብዮ እገምታልሁ። እነሱም የአውሮፓዉያን ፍልፍስና እና የባንቱ ፍልስፍና ተብለው በትምህርቱ ገበታ ላይ ለአሉ ተማሪዎች በአልፉት አምሳ ዓመታት ዘመን ዉስጥ ጀምሮ ሲሰጥ የኖረ ትምህርት ነው። ተማሪዎችም በትጋት ተከታትለው የአለምንም ጥያቄ ተቀብለዉታል። ባንቱ ማለት ለጥቁር አፍሪቃ ቋንቋዎች በአንድነት የሚጠሩበት ስም ነው። ባንቱ የጥቁሮችን ሕብረተሰብ አጠቃሎ የያዘ ቋንቋ ነው፤ ለመጀመሪያ ግዜ የባንቱ ፍልስፍና በማለት የሰየመው ፕላሲድ ቴምፕል የሚባል ወንጌላዌ ክርስትናን ለማስፋፋት ከአውሮፓ ወደ አፍሪቃ አህጉር የሄደ ቄስ ነው። ቄሱም ከእግዚአብሒር የተላኩህ መልዕክትኛ ስለሆንክ አፍሪቃዉያን ትምህርቲን ተቀብለው እንድያምኑ ከላይ የተሰጠ ቃል ነው በማለት ፍልስፍና በባንቱ ቋንቋ ምን ማለት እንደሆነ አስተምሮአል። ይህንንም አፍሪቃዉያን አምነው ተቀብለዉታል፤ በቲምፕል አባባል በባንቱ ቋንቋ የሰዉነት አካል "ኀይል" ነው፤ ከሕሊናዌነት ጋር ምንም ግንኙነት የለዉም፤ እምነቱም ሕሊናብስነት ስለሆነ የሚጠቀመው "ኀይልን" ብቻ ነው፤ "ከኀይል" ዉጪ ሊላ ነገር አያውቅም ይላል። በአንፃሩ ደግሞ የአውሮፓውያን ፍልስፍና መሰረቱ ሕሊናዉነት ነው፤ የአውሮፓዉያን የሰውነት አካል ከሕሊናዌነት ጋር የተያያዝ ስለሆነ አይነጣጠሉም፤ ኀይሉም የሕሊንዉነቱ ተገዢ ሰለሆነ ሕሊናብስነት የለዉም በማለት ሁለት የተለያየ የፍልስፍና መዋቅር አስቀምጦልናል፤ የአውሮፓዉያን ፍልስፍና እና የባንቱ ፍልስፍና፤ ስለዚህ ነው ደስካርትና ዘርዓ ያዕቅብ አንድ መሆን አይችሉም የተባለበት።*

*እንግዲህ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ሁለት የፍልስፍና ግብረ ኀይል ከመረመርን በኋላ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለን መጠየቅ ግዴታ ነው፤ ይህን ጥያቄ መጠየቅ ከአልቻልን አውሮፓውያኖች እንድሚሉት እውነትም ሕሊናቢስ ነን ማለት ነው። በመሰረቱ ይህ ሊሆን አይችልም፤ፍጥረት አንድ ነው፤ የሰው አካልና ሕሊናው አይለያዩም። ለዚህም በቂ መረጃ ሆኖ የሚሰጠው የታላቁን አፍሪቃዌ ፍልስፍና ታሪክ ነው። የዚህ ታላቅ ፈላስፋ ታሪክ የሚጀምረው በትንሽ ቦታ አክሲም በምትባል መንደር ነው። አክሲም የምትገኘው በምዕራብ አፍሪቃ ጋና በሚባለው አገር ዉስጥ ነው፤ የፈላስፋው ስም "አሞ" ይባላል፤ የተወለደውም በ1700 ዓ ም አካባቢ ነው ተብሎ ተገምቷል፤ ጀርመን አገር የሚገኝ ብረንዊስክ ዎልተንባትል በሚባል ቤተክርስቲያን መዝገብ ዉስጥ ተጽፎ የሚገኘው ሰነድ እንደሚያመለክተው "አንቶን ዊልሃልም አሞ" ተብሎ በ8 ዓመቱ ክርስትና ተነስቷል። "አሞ" ከአፍሪቃ ወደጀረመን እንዴት እንደተወሰደ በጽሑፍ የሚታወቅ ነገር የለም፤ ሆኖም ክርስትናዉንም ሆነ ትምህርቱንም የተከታተለው አንድ የጀርመን መስፍን ቤት ዉስጥ ሆኖ ነው፤ አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች እንድሚሉት የብረንስዊኩ*

*ዎልፈንባትል መስፍን “አሞንን” ከጋና ያስመጣው ቅስና ተቀብሎ ክርስትናን አፍሪቃ ዉስጥ እንዲያስተምር ነው ይላሉ፤ ነገር ግን በጽሑፍ የተገኘ መረጃ የለም። “አሞን” በመስፍኑ ቤት እንደቤተሰብ ሆኖ በታላቅ እንክብካቤ ጀርመን ዉስጥ አሉ ከተባሉት ታዋቂ ትምህርት ቤቶች በመከታተል በታላቅ ማዕረግ ትምህርቱን አጠናቋል፤ በቋንቋም ልዩ ስጦታ ስለነበረው የተለያዩ የአውሮፓዉያን ቋንቋዎች አጥንቷል፤ የመጨረሻውንም የፍልስፍና ዶክቴሪት የጻፈው በላቲን ነው። እንግዲህ “አሞንን” ታላቅ ከአደረጉት ውስጥ ሁለቱ የፍልስፍና ጽሑፎች ናቸው፤ አንደኛውና ታዋቂው ጽሑፉ “ስሜት በሕሊና ሳይሆን በአካል ዉስጥ ይገኛል” በማለት የጻፈው “ንጥረ ነገር” ነው፤ “አሞ” በታላቅ ደረጃ ተመራቂ ስለሆነ ታዋቂው በሆነው ሔል ዩኒቨርስቲ በፕሮፌሰርነት ማዕረግ ተቀጥሮ በሚያስተምርበት ግዜ ለተማሪዎቹ የሚያስተምረው ስለ ቁሳዊ አካልና ሒሊና ባሕራያት ነበር፤ ይህም ትምህርቱ በተማሪዎች ዘንድ ታላቅ አክብሮትን አስገኝቶለት ነበር። በ1738 ዓ ም ባቀረበው ጽሑፉ “በተረጋጋ መንፈስ የሚጻፍ ትክክለኛ ፍልስፍና” በማለት ሸፍጠኞችን ዘረኞችንና የኃይማኖት አክራሪዎችን በሚገባ ተችቷል፤ የፈረንሳዩውን ፈላስፋ ደስካርት የጻፈውን “ሁለት ፍጥረት” በመቃወም ስለ ቁስ አካል ታሪካዊ ሄደት በንጥረ ነገር አስረድቷል። ስለ ቁስ አካልም ሲፈላስፍ እንዲህ ይላል “ያለ ነገር ይኖራል፤ ሊኖር የሚችለውም በእንክብካቤ ነው፤ ለእድገትም እንክብካቤ ያስፈልገዋል፤ እነዚህ ሁሉ መሆን የሚችሉት ይህ “ሁኔታ” ሲፈጠር ብቻ ነው” ይላል። “ሁኔታ” የሚለው “የአሞ” ሁለተኛው “ንጥረ ነገር” ነው። “አሞ” በጀርመን ፍልስፍና ታሪክ ዘመን ሁለት “ንጥረ ነገሮችን” የጻፈ ብቸኛው ፈላስፋ ነው። ይህም ሆኖ ያሳደገው መስፍን ስለሞተ በፍልስፍናው ደስተኛ ያልሆኑ የኃይማኖት አክራሪዎች ከሚያስተምርበት ወንበር አስነስተው ከአገር እንዲባረር አድርገዋል። “አሞ” ወደ ትውልድ አገሩ አፍሪቃ ተመልሶ ብዙም ሳይቆይ በተወለደ 56 ዓመቱ አርፏል። “አሞ” ተወዳዳሪ የሊለው ታላቅ ፈላስፋ ነው። አውሮፓውያን ሊላዉን ሕሊናቢስ ማለት አይችሉም። “የአሞ” ትምህርት ጀርመንም ሆነ ሊላ አገር አፍሪቃዉነቱንና ሕሊናዌነቱን አይቀይረውም፤ ሰው ስለሆነ ሰው የሚያደርገዉን ሁሉ የማድረግ ፋጡራዊ ሕግ ስለሆነ ነው፤ ይህ የተባለበት ምክናያት አንባቢ ይህንን አስታውሶ ለወደፊቱ ውይይታችን እንዲረዳው ይጠቅማል በማለት ነው።*

*“አሞ” እንደሚለው ፍልስፍና “በተረጋጋ መንፈስና በትክክል” መጻፍ አለበት፤ ይህም ማለት ፍልስፍና አውነትና ትክክል ነው፤ በተጨማሪ ፍልስፍና ለሰው ልጅ ጠቃሚ ነው፤ ለሰው ልጅ ጠቃሚ ከአልሆነ ግን በሁለተኛው ጽሑፉ ላይ እንደገለጸው “ሸፍጠኛ” “ዘረኛ” “ወገንተኛ” ይሆንና ለሰው ልጅ አጥፊው ይሆናል። ለምሳሌ አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኒታ አንድ ታጋይ ሲፈላስፍ እንዲህ ይላል፡ “እኔ የምታገለው አማራን መልሼ ሥልጣን ላይ ለማውጣት አይደለም”። የአማራ ገዥነት በዘመነ ጉጉግ ማንጉግ ጌዜ የኢትዮጵያ ወጣት ተማሪዎች “በሸፍጠኛ ፈላስፋዎች” ገና በእንጨቅላነታቸው በተጠለፉበት ዘመን የተወራ ወሬ ነው፤ የጄሬናል ቫረቴሲ የዱቼ ሙሰሌኔ የቫንዳ የልጅ ልጆችና አሽከሮቻቸው ፕሮፓጋንዳ ነው። አሁንም እነኛ “ሸፍጠኛ” “ዘረኛ” እና “ወገንተኛ” ፈላስፋዎች ለእናት ኢትዮጵያ የሞቱላት ጀግኖች እየተባለ ዝክረ ነገራቸው ሲነገር የሚያሳየው አንድ ሕብረተሰብ ሊቆጣጠር ከሚችለው በላይ ሆኖበት ኀዘኑን ከመግለጽ በላይ ያለበትን “ሁኔታ” ሊያቀውም ሊለውጥም አለመቻሉን ነው-- “አገሪ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤ የምተለሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ” እያለ “የሁኔታ ተገዥ” ሆኖ ቀርቷል። ልጆቿን የገድሉ ነፈሰ ገዳዮች ዛሪ “ኢትዮጵያ አገሬ እንምትልሽናል እንስባበርልሻለን” እያሉ ሲዛበቱባት ማየት አስገራሚ ነው። ዕውነትን ያልተከተለ ፍልስፍና ሕበረተሰብን ያጠፋል፤ በመለስ ዜና እና በኢሳኢያስ አፈወርቂ ልዩ ትዕዛዝ የአማራ ሕብረተሰብ እንደበግ ታርዷል፤ በገደል ከእነፍሱ ተወርዉሯል፤ ገበሪው ሲቱ ሸማግሊው ሕፃናቱ እቢቱ ዉስጥ ቷጉረው በእሳት ነድዋል። መለስ ዜናዌ በለሐጩ ያዝረከረከው መርዝ ደግሞ እንደራዕይ ተቆጥሮ ይነገርለታል። የጀርመኑ ሄትለር ይሁዲዎችን በጋዝ ሲያቃጥል ለሰው ልጅ “የመጨረሻው መፍትሄ” ብሎ ነው፤ ግን ይሁዲ ሰው ስለሆነ የእሱ ጥፋት ደግሞ እንደመፍትሄ ከሆነ የሰው ልጅ ሁሉ መጥፋት ይኖርበታል፤ ይህ ከአልሆነ ግን መፍትሄ ያለው ሊሆን አይችልም። ጥራት የሊለው “የወገንተኛ ፍልስፍና” የሚባለው ይህ ነው፤ ትልቅ የፍልስፍና ድሕነት፤ ግብዝነትና ጨቃኝነት። ማከቬሊ ሥልጣን ለመያዝ የተጠቀመው ፍልስፍና የሰውን ልጅ ሰብአዊ መብት በመጣስ ነው፤ ገድሎም አታሎም ሰርቆም አስሮም ሥልጣን መያዝ ተገቤ ነው ስለሚል ሕብረተሰቡን አሳምኖ ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርጓል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ለአልፉት አንድ መቶ ዓመታት በሥልጣን የወጡ አምባገነኖች ገድለው አስረውና አታለው ነው። ከላይ የተጠቀሰው ሰው የሚታገለው ለሥልጣን እንጂ አገርን ነፃ ለማውጣት አይደለም። በዚሁ አይነት የሥነ ምግባር ፈላስፋዎች የፈልሰፉትን አቶሚክ ቦምብ አገልግሎቱ ለሰው ልጅ እድገት ብቻ እንዲሆን ከመንግስት ጋር ለማድረግ ያቀዱት ውይይት ሊሳካ አልቻለም፤ከግኙቱ በኋላ አጠቃቀሙን የሚወስነው መንግስት እንጂ ሊላ አካል ያለመሆኑን ሲያውቁ የተፈጠረው “ሁኔታ” ከቁጥጥራቸው ውጭ ስለሆነ የፍልስፍናው ዉጤት ጥፋት ሆነ። በዚህ ፍልስፍና የተግኘ ግኝት ልክ የዛሪ 70 ዓመት ከአንድ መቶ ሺህ በላይ ሕዝብ በሆሮሽማና በናጋሴ ከተማዎች እንዲጠፋ ምክናያት ሆኗል። ጥራት የሊለው ፍልስፍና የሚያስከትለው ጉዳት የቱን ያህል እንደሆነ አንባቢ በአንክሮ እንዲመለከተው ያስፈልጋል። በዘመኑ የዘርዓ ያዕቆብን ፍልስፍና ሊቃዉንቱ በተረጋጋ መንፈስ ቢወያዩበት ኖሮ ምናልባት ሕብረተሰባችን አሁን ያለበት “ሁኔታ” ዉስጥ ላይኖር ይችል ነበር ብዮ እገምታለሁ፤ ይህ እንደ መላ የተሰጠ ግምት ነው።*

*እንግዲህ የፍልስፍናን ትርጉሙን ታሪካዊ ሄደቱን ጥቅሙን እና ጉዳቱን በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ የፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌን "ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ" በሜል መቅድም ላይ የሰጡትን አስተያየት በአንክሮ እንመለከታለን። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው አስተያየታቸዉን ለማረም ሳይሆን በዘርዕ ያዕቆብ ፍልስፍና ላይ የተደረገዉን ውይይት በተመለከተ ይሆናል። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ በአስተያየታቸው መቅድም ላይ የጻፉት በሶወስት ደረጃ ተከፍለው በተሰጡት ደንብ መሰረት አይደለም፤ ይህ ደንብ የዜህ ጸሐፊ ሳይሆን የሥነ ጽሑፍ መሰረታዊ መነሻ ነው። አንባቢ በትኩረት ተመልክቶ ከሳቸው ጽሑፍ ጋር አመሳክሮ ምስክርነቱን ሊሰጥበት ይገባል፤ በአንደኛ ደረጃ ማየት ያለብን መጽሐፉ ባለቤትም አርዕስትም አለው። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌም ይህንን እንደሜቀበሉ አምናለሁ፤ በዚህ ላይ ከተስማማን በዘርዕዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ላይ የአደረጉት ውይይት የሚጀምረው እንዲህ በማለት ነው፡*

*ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ በሚባል ስም የሚታወቀው የወርቄ የሕይወት ታሪክ*

*መቅድም*

***አንድ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (Padre Giusto da Urbino) የሚባል የካቶሊክ ሚሽኔሪ ደብረ ታቦር (ደምቢያ) ላይ ሆኖ በፌብሩዋሪ 1853 ዓ.እ.(=1844 ዓ.ም.) የአንድ የግዕዝ ድርሰት ሁለት ቅጂዎች በዚያን ጊዜ ፓሪስ ለሚኖረው አንቷን ዳ'አባዲ (Antoine d'Abbadie) ይልክለታል። አንቷን ዲ.አባዲ በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ መጥቶ ዛሬ ከታላቁ የፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ካሉት የግዕዝ መጻሕፍት አብዛኞቹን ሰብስቦ ያመጣ ተመራማሪ ነበር። አንቷን ዲ.አባዲ እነዚህን ሁለት ቅጂዎችም በዚያው በታላቁ ቤተ መጻሕፍት ከትቷቸው፥ አንደኛው በስሙና በቍጥር፥ D'Abbadie 215፥ ሁለተኛው D'Abbadie 234 በመባል ይታወቃሉ። .ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ. የሚባለውን የኢትዮጵያ ጥናት ሊቃውንትን ያጨቃጨቀውን የወርቄን የፍልስፍና ትችት የያዙ እነዚህ ሁለት ቅጂዎች ናቸው። ጭቅጭቁ ምን እንደሆን ያልሰማ እንዳለ፥ በአጭሩ እንዲህ ነው፤ ይህ ድርሰት በዓሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመት የኖረ ዘርአ ያዕቆብ የሚባል ኢትዮጵያዊ የደረሰው አይደለም፤ ፓድሬ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (Padre Giusto da Urbino) ሚሲዮናዊ ስለሆነ ማንነቱ እንዳይታወቅ .ዘርአ ያዕቆብ. የሚል የብዕር ስም አውጥቶ የደረሰው ነው የሚል ነው። ቅጂዎቹን ሊያያቸውና ሊመረምራቸው የሚፈልግ መታወቂያቸውን ጠቅሶ ፎቶግራፋቸው ከፓሪስ እንዲላክለት መጠየቅ ይችላል። ጭቅጭቁ የተካሄደባቸውን ምንጮች ከዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ዘርዝሬያቸዋለሁ።***

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ በምን ምክናያት "ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ" የሚለውን መጽሐፍ በጁስቶ ዳ አርቢኖ አማካይነት የሚጀምሩት? ፈረንሳዩ አንቷን ዳ አባዲ በአባሪነት የቀረበበት ምክናያት ለምንድነው? ደግሞስ "የኢትዮጵያ ጥናት ሊቃዉንት [የዉጭ አገር መምህራን መሆን አለባቸው] ያጨቃጨቀዉን" የሚሉት? ምን አገባቸው በኢትዮጵያ ፍልስፍና ላይ? ለምንስ ወዳጃቸው አቶ አሰፋ ገብረማርያም እንደጠየቁት ትርጉሙን ተርጉመው ለአንባቢ አያቀርቡም ነበር? አንባቢ ከላይ በአባሪነት የቀረበውን መረጃ ተመልክቶ አስተያየቱን ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ለዘርዕዓ ያዕቆብ ፍልስፍና መጽሐፍ መነሻ ሊሆን አይችልም፤ መነሻ ሊሆን ቀርቶ በዋቢነት መቅረብ አይችልም፤ ምክናያቱም መረጃ የሊለው ወሬ ነው። በተጨማሪ ከላይ በአጭሩ እንደተማርነው ፍልስፍና "በጭቅጭቅ " አይገኝም፤ ፕሮፌሰሩ የቋንቋ መምህር ስለሆኑ የችሎታ ማነስ ሳይሆን የቃላት  አመራረጥ ክስተት ይሆናል ብዮ እገምታለሁ፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ በመቅድማቸው መነሻ አድርገው የሰጡት መሰረተ ቢስ ከመሆኑም በላይ የአንድ ቅርስና ባለቤትነትን የሚጻረር ነው። ለዚህም መረጃ የሚቀጥለውን ትንተና በትኩረት ይመልከቱ፡*

> *ከዚያም አልፎ ተርፎ፥ ድርሰቱ በክርስቲያኖች ዓይን ሲታይ ህርጥቅና (heresy) ስለሆነ፥ .እንዳልታወቅ ዘርአ ያዕቆብ በሚል በብዕር ስም የጻፍኩት እኔ ነኝ. ሳይል አልቀረም። የጻፈው ማስታወሻ ተገኘተብሎ፥ በካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ መሪነት ድርሰቱ ከዘርአ ያዕቆብ (ከወርቄ ማለት ይሻላል) ተወስዶ ለጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ተሰጠ። ሌሎች ተመራማሪዎችም፥ በተለየም ኦይገን ሚትቮኽ (Eugen Mittwoch) የኮንቲ ሮሲኒን ፍርድ አጸኑ። ፓድሬው በወርቄና በድርሰቱ ላይ ያደረሰውን በደል እስከዛሬ ከሊቃውንቱ አእምሮ መፋቅ አልተቻለም። የኮንቲ ሮሲኒ አቋም ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ። የዘርአ ያዕቆብን ስም ሰምተው የማያውቁ ሁሉ ፈላስፋ ነው ስለተባለ ብቻ ኢትዮጵያዊ እንደነበረ መሰከሩለት።*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ትኩረታቸው ትርጉሙ ላይ ስለሆነ የዘርዓ ያቆበን ሐተታ በሚገባ ተመልከተዉታል ማለት ያስቸግራል፤ ትርጉሙን ከጨረሱ በኋላ በቀጥታ ወደራሳቸው አስተያያትና በጽሑፉ ላይ ዕውቀት አላቸው የሚሏቸውን ሊቃውንት ትንትን ውስጥ የገቡት፤ በመጀመሪያ የዘርዓ ያዕቆብ ጽሑፍ መታየት ያለበት በሌላ ዓይን ሳይሆን በርሳቸው መሆን ነበረበት፤ እሳቸው እንዳሉት “ህርጥቀኛ” [ሃይማኖተ ቢስ] የሆነበትን ምክንያት ከመጻሐፉ ጠቅሰው ለመረጃ እንዲሆን ማቅረብ ነበረባቸው፤ ግን ወሪ ሰምተው “ህርጥቅኛ [ሃይማኖተ ቢስ] ያሉት፤በሥነ ጽሑፍ እንደዚህ ዓይነቱ ክስተት አይፈቀድም። ሁለተኛ ዘርዓ ያዕቅብ ስለ ሃይማኖቱ ሲመራመር እራሱን እንደ “ህርጥቀኛ” [ሃይማኖተ ቢስ] አድርጎ አልተመለከተውም፤ አንባቢ በትኩረት መመልከት ያለበት ፕሮፌሰሩ ዘርዓ ያዕቆብ የጻፈውን “ሐተታ” በደንብ አድርገው እንዳልተመለከቱት ነው፤ በጽሑፉ ያልተስማሙ ደብተራዎች “ህርጥቅና” [ሃይማኖተ ቢስ] ነው ስለ አሉ ምናልባት ሳይሆን አይቀርም በማለት ነው የደመደሙት፤ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ እና ሚቶቮኽ ያሏቸው ሊቃውንት ለምን በዋቢነት እንደተጠቀሱ ግልጽ ነው። እነዚህ የውጭ አገር ሊቃውንት ለእኛ ኢትዮጵያውያን ለዕውቀታችን መለኪያ አድርገን ስለምንመለከታቸው የእነሱን ስም ዋቢ አድርገን መጥራት ግዴታችን ስለአደረግነውና ስማቸው በዋቢነት ከአልተጠቀሰ ውይይቱ ዋጋ ሊኖረው አይችልም ብለን ስለምናምን ነው። መጽሐፉ ከተጻፈ ሁለት መቶ ዓመት በኋላ የውጭ አገር ሊቃውንት ወደአገራችን መጥተው በአገሬው ሰው የተጻፈዉን መጽሐፍ ጻፈው አልጻፈው ማለት ብቃቱ እንደሊላቸው ስለማናውቅ ብቻ ነው። ፕሮፌሰሩ ከሁለቱም ሊቃውንት በበለጠ ስለአገራቸው ዕውቀት አላቸው ብዮ እገምታለሁ። ነገር ግን የእነዚህ ሊቃውንት ስም  መጠቀስ የሳቸውን ዕውቀት ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ስለሚገመት ነው እንጂ ዘርዓ ያዕቆብ የተመለከተውን የአገሩን “ሁኔታ” እነሱ በበለጠ ያውቁታል ማለት አይደለም። ፕሮፌሰሩ ይህንን “ሁኔታ” በአንክሮ ተመልክተው ማወቅ ግዴታ ነበር። በእርሳቸውም ዘመንም ሆነ  በአሁኑ ታዋቂ የውጭ አገር ሊቃውንትን በዋቢነት ማቅረብ ዕውቀታችንን ከፍ ያደርገዋል ብለን ስለምናስብ ነው። እዚህ ላይ አንባቢ መመምልከት ያለብት ታዋቂ ሊቃውንት አይጠቀሱ ማለት ሳይሆን ሥራዓትን ተከትሎ ይሁን ለማለት ነው። ግን እንደጡት እናትና አባት ሆነው ሁሉንም ነገር እነሱ እንዳሉት ማለት ገደብ የሊለው ጥገኝነት መፍጠር ይሆናል። በአጭሩ ኮንቲ ሮሲኒ በዘርዓ ያቆብ ጽሑፍ ላይ አስተያየትም ሆነ ትችት የማድረግም ብቃትም  ሆነ ችሎታ የላቸውም፤ ወደአገራችን የመጡት የተለያዩ ቋንቋችንን አጥንተው ልዩነታችንን አጉልተው ለማሳየት ነው። በተጨማሪ አንድ የኢትዮጵያ ደብተራ እንደዚህ ዓይነት ጽሑፍ ሊጽፍ ብቃት የለዉም በለው ስለሚያምኑ ጸሐፊው አውሮፓውያን ሳይሆን አይቀርም በሚል መላ ምት ያወሩት ወሬ ነው። ወሬ በዋቢነት ሊቀርብ አይችልም፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ  እዚህ ላይ ሊስማሙ ይገባል።*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ስለ ዘርዓ ያቆብ ፍልስፍና ምን ለማለት አሰበው እንደሆነ ላማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ “የኮንቲ ሮሲኒ አቋም ኢትዮጵያንን አስቆጣ ...........ዛሬ የዘርአ ያዕቆበን ሰምተው የሚያውቁ ሁሉ ፈላስፋ ነው ስለ ተባለ ብቻ ኢትዮጵያዊ እንድሆነ መሰከሩለት” ይላሉ፤ ደግሞ በትንትናቸው ላይ “ድርሰቱ በክርስቲያኖች ዓይን ሲታይ ህርጥቅና” ነው ይላሉ፤ ጽሁፋቸው ጥራት የለዉም፤ ግደየለሽ ይታይበታል፤ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ኢትዮጵያዊያን ፋላስፋዎች አቋሟቸው ከኮንቲ ሮሲኒ አይለይም፤ ዘርዓ ያዕቆበ የመጻሕፉ ደራሴ መሆኑን የሚያጠራጥር አይመስለኝም፤ ፕሮፌሰሩም በዚህ ይስማማሉ፤ ዶክተር አምሳሉ አክሊሉ እና አቶ ዓለማየሁ ሞገስ የኮንቲ ሮሲንን ወሬ በመቃወም የዘርዓ ያዕቆብን ጸሐፊነት አረጋግጠዋል፤ ደግሞም አንድ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ሲገኝ የአገር ሕሊናዊነት ስለሆነ የወሰዱት አቋም ትክክል ነው፤ በአንፃሩ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ የዘርዕ ያዕቆብን ፈላስፋነት ለማመን አጥብቀው የተቸገሩ ይመስላሉ፤ ምክናያታቸውንም ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ፤*

*ፍልስፍናው በመሠረቱ የሱ መሆኑን ግን በሁለት ምክንያቶች እጠራጠራለሁ። አንደኛ፥ ተፈላስፎ የእግዚአብሔርን መኖር ያመነው፥ የሚያየው ፍጡር ሁሉ ያለፈጣሪ አይፈጠርም ከማለት ተነሥቶ ነው። ይኸንን ከቅዱስ ቶማስ አኩይናስ (Thomas Aquinas, 1225-1274) ጀምሮ በካቶሊኮች ዘንድ የገነነ .ምክንያትና ውጤቱ (The law of causality) አስተሳሰብ ወርቄ የካቶሊኮቹ ተማሪ በነበረበት ጊዜ አልሰማውም ማለት ያስቸግረኛል።*

*ከላይ በአጭሩ ስለ ፍልስፍና ስለተወያየን አሁን አዲስ ነገር አይሆነብንም፤ የፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌም መጠራጠር አያስደንቅም፤ ይህ ትክክለኛ አቋማቸው ነው። ለውይይት ያህል እንደገና "አም " የተባለዉን የጋናዉን ፈላስፋ መጥቀስ አስፈላጊ ነው። "አም" በሕፃንነቱ ከአገሩ ወደ ጀርመን ሄዶ ታዋቂ ፈላስፋ ሆኗል፤ ይህም የሚያሳየው የተመቻቸ "ሁኔታ" ስለአገኘ ተመራምሮ እንደደረሰበት አካሉ ከሕሊናዉነቱ ጋር ተባብሮ "ንጥረ ነገሮችን" በማግኘቱ ታላቅ ከተባሉት ፈላስፋዎች አንዱ መሆኑን አረጋግጠናል፤ "የአም " አካልና ሕሊናዊነት የአፍርካም የጀርመንም አይደለም፤ የሰው ልጅ አካልና ሕሊና ነው፤ ይህ ፍጥረት ስለሆነ ማንም ሊወስደው አይችልም፤ ዘርዓ ያዕቆብና ቶማስ አኩይና ሰው ስለሆኑ ፍጡራዊ የሆነ አካልና ሕሊና አላቸው፤ ሃይማኖታቸው ተዋሕዶም ሆነ ካቶሊክ የአካልና የሕሊና ለዉጥ አያመጣባቸውም፤ "ሁኔታ" ግን ትልቅ ልዩነት ያመጣል፤ ለምሳሊ ዶሮ እንቁሏሏን ተንከባክባ አስፈላጌዉን ሙቀት ከአልሰጠች ጫጩቶቹ አይፈለፈሉም፤ ፕሮፌሰሩ የሁለቱን ፈላስፋዎች "ሁኔታ" መርመረው ግኝታቸውን ቢሰጡን ኖሮ ጥሩ ነበር፤ ይህንን አላደርጉም፤ ያደረጉት እንደሊሎቹ ኢትዮጵያውያን ፈላስፋዎች ዘርዕ ያዕቆብ አውሮፓዊያን ስለአልሆነ ሊፈላሰፍ አይችልም ነው፤ በፕሮፌሰሩ አስተሳሰብ ዘርዓ ያዕቆብ የሚያንጸባርቀው ሃሳብ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት የነበረዉን ዝነኛ ፈላስፋ ቶማስ አኩይናን ነው ይላሉ፤ ፕሮፌሰሩ በዚህ ላይ የአላቸው አቋም ጠንካራ ነው፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ አሉ የተባሉ ታላላቅ መጻሕፍት ሁሉ ከውጭ በትርጉም የተገኙ ናቸው በማለት አጠንክረው ስልሚያምኑ ፍልስፍና ለኢትዮጵይዉያን እንግዳ ነገር ይመስላቸዋል። ለዚህ ነው አጥብቀው የተጠራጠሩት። "ሁኔታ" ወሳኝ ነው፤ ስለዚህም ነው ዘርዓ ያዕቆብ በብዕር ስም ተደብቆ ጽሑፉን የተወልን፤ ነገር ግን ይህንን "ሁኔታ" ከግንዛቤ አስገብቶ "ሁኔታን" መቀየር ሲገባ ውይይቱ ሌላ ሆነ፤ እንግዲህ እንዴት ሆኖ ነው "ሁኔታ" ሊስተካከል የሚችለው? ከየትኛው መጽሐፍ እንደሆነ ባላስታውሰም ጽሑፉ ግን ከአእምሮዮ አለ፡ መጽሐፉ እንዲህ ይላል "ወርኢኩ ጽሑፍ በላዕሊሆሙ እስመ ትውልድ ትኢብስ እስከ ትትነሣእ ትውልደ ጽድቅ ወአበሳ ትትኃጉል ወኃጢአት ትትለሑሱ እምዲበ ምድር ወኩሉ ሠናይኢ ኢይመጽእ።" "ጻድቃንና ብሩክ የሆነ ትውልድ እስኪመጣ ድረስ ጥፋት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተልስለፋል፤ ግን መልካሙ ትውልድ ሲነሳ በምድር ላይ የአሉ መጥፎ ነገሮች ተወግደው መልካም "ሁኒታ" ይመጣል" [ትርጉሙ ቃል በቃል አይደልም]። እዚህ ላይ አንባቢ በአንክሮ መመልከት ያለበት ዘርዓ ያዕቆብ የአለንበትን "ሁኔታ" በተለያየ መንገድ ሲነግረን መስማት አልቻልንም። እዚህ ላይ ፕሮፌሰሩ "የሁኔታ" ጉዳይ መሆኑን ስለአልተገነዘቡ "ሁኔታን" ለመለወጥ ምንም ያደረጉት አስተዋፃኦ የለም። መልካሙ ትውልድም መቺም እንደሚመጣ አይታወቅም፤ ነገር ግን እኛ የምናውቀው ትውልድ አጥፊ ትውልድ ስለሆነ ፍልስፍናዉም ጉግ ማንጉግ ነው፤ በዘመናችን የነበርንበትን "ሁነታ" እንለውጣለን ተብሎ ወደ ባሰ መጥፎ "ሁነታ" ገብተናል። የዚህ ታሪክ በአጭሩ እንደዚህ ነው፤*

*ይህንን "ሁኔታ" ለመግለጽ ሰፊ የሆነ ጥናት ያስፈልጋል፤ ነገር ግን ለዚህ ውይይት ይረዳል የተባሉትን በአጭሩ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፤ የኢትዮጵያ አገራችን ታሪክ ማለቂያ የሊለው "ሁኔታዎች" ከቁጥጥር ዉጭ ሆነው የሆነውንና የአልሆነውን ነገር ሲነገርባት የኖረች አገር ነች፤ ጥንታዊት ነች ግን የጥንታዊነታ ቅርስ አልተጠበቀም፤ በተለያየ "ሁኔታ" ጠፍቷል፤ በታሪክ ከ3ት ሺህ እስከ አንድ መቶ ዓመት ነው ተብሎ ተገምቷል፤ ግን 3ት ሺም አንድ መቶም የሚሉ "ሁኔታዎች" ስለሚፈራረቁ በትክክል የታሪኳ ዘመን አይታወቅም፤ ክርስትናን በአገር ደረጃ የተቀበለች የመጀመሪያዋ ነች ይባላል፤ ነገር ግን አገልግሎቷ ለፖለቲካ አካል ስለሆነ ክርስትናን የሚያመለክት ምንም ነገር የለም፤ ፕሪስትር ጆን የሚባል ፋላስፋ ንጉሥ የሚገዛት አገር ስለነበረች ፍትሕ የምላቧት ነች ይባላል፤ ነገር ግን የአምባ ገነኖች መጨፈሪያ ስለሆነች ፍትሕ ናፋቂ ሆና ቀርታለች፤ ከሁሉ የሚበልጥ ታሪክ አለን ብለን እናምናለን፤ ነገር ግን በምን ከሊላው እንደምንበልጥ የምናሳይበት ነገር የለም፤ ለምንስ ከሊላው መብለጥ እንዳለብንም አናውቅም፤ ለምንስ እንደሊላው ጢነኛ ሰው አንሆነም? መብለጥስ ለምን አስፈለገ? ከሁሉ በላይ ክርስቲያን፤ ከሁሉ በላይ አዋቂ፤ ከሁሉ በላይ ኮሚኒስት መሆን አስፈላጊ ነው? እንደዚህስ ያሉ "ሁኔታዎች" ለጢንነታችን ጥሩ ነው? በእንደዚህ የአለ ታሪክ "ሁኔታዎች" የሚፈራረቁባት አገር ነች፤ ለመረጃ ከ1970 እስከ 1991 የተደረጉትን "የሁኔታ" ለዉጦችን መመርመር ጠቃሚ ነው። ጠቃሚነቱም ኢትዮጵያ በረጅም ታሪኳ ለመጀመሪያ ግዜ የኀሳ ኮሮጆ እንድትሆን የተደረገበትን "ሁኔታ" መፈጠሩን ነው። ቤነዚህ ሃያ ዓመታት ዉስጥ የተደረጉት "የሁኔታ" ሂደት በታሪክ አጋጣሚ ሳይሆን*

*በስሊት ተቀነባብሮ የተፈጠረ ነው። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዚ የአውሮፓውያንን የጦር ኀይል ተቋቁማ ድል ስለናሳች መቀጣት አለባት በማለት የተነሱ ኀያላን መንግሥት ሴራ ነው አሁን ያለንበትን "ሁኔታ" የፈጠረው፤ የጂሪናል ቫረተሪ ሕልም እውነት የሆነበት "ሁኔታ" ፤ በአደዋ ጦረነት ግዜ የሚኒልክ ጦር በጎሳ ፍርክስኩሱ ይወጣል እያለ ስያልም ነው "የኦሮሞ ፈረሰኛ" ድርምጥማጡን ያጠፋው፤ ስለዚህ ነው ኦሮሞ የኢትዮጵያ አካል አይደለም የተባለው? ስለዚህ  ነው የአማራ ዘር መጥፋት አለበት ተብሎ የተፈረደበት፤ በአጭሩ የሆነው እንዲህ ነው፤ በእነዚህ ሀያ ዓመታት ግዜ ኢትዮጵያ የሚባል ስም እንዳይነሳ ተደርጎ የነበረዉን አስከፊ "ሁኒታ" ለመለወጥ የሚደረገው ስብስብ ሁሉ በሌላ መሆን ግዲታ ነበር፤ የአፍሪቃ ቀንድ ስብስብ፤ የምስራቅ አፍሪቃ ጉባኢ፤ የትግራይ ነፃ አውጭ ፤ የኤርትራ ነፃ አውጭ ፤ የኦሮሞ ነፃ አውጭ፤ በመባባል ነው "ሁኔታው" የተፈጠረው፤ በኢትዮጵያ ስም መሰባሰብ ፍገጽሞ ክልክል ነበር። ዉጢቱም ኢትዮጵያ  የጎሳ ማሕደር ሆና አገርንቷ ቀርቶ የክልል መሪት መሆኗ ነው።፡ ይህንን ነው የጉግ ማንጉግ ፍልስፍና ያመጣብን፤ ዘርዓ ያዕቆብም ፈላስፋ ሊሆን አይችልም የተባለበትም ዋና ምክናያት ኢትዮጵያዉነትን ላለመቀበል ነው፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌም ባለማወቅ ኢትዮጵያነትን ከሚያጠፋ ኀይል ጋር የተሰለፉ ይመስላል። በመጨረሻ ፕሮፌሰሩ በሰጡት አስተያየት ላይ አጠር ያለ ግንዛቤ ከተደረገ በኃሏ ወደሁለተኛው ዘርዓ ያዕቆብ ውይይት እንገባለን። ፕሮፌሰሩ ስለ ዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ሲፈላሰፉ እንዲዚህ ይላሉ፤*

> *ሁለተኛ፥ ከሁሉም የሚገርመው .የኮከቦችን ቍጥር፥ ርቀታቸውን፥*
> *ስለርቀታቸው ትናንሽ የሚመስሉን ትልቅነታቸውን ማን ያውቃል?.*
> *ማለቱ ነው። ኮከቦች ትናንሽ የሚመስሉት በርቀታቸው ምክንያት*
> *መሆኑን በቴለስኮፕ እንጂ በመፈላሰፍ የሚደረስበት አይደለም።*
> *ይኸንንም የካቶሊኮቹ ተማሪ በነበረበት ጊዜ ከእነሱ አፍ አልሰማውም*
> *ማለት ያዳግተኛል። ዋናው ቁም ነገር ግን ዘርአ ያዕቆብ የሚነግሩትን*
> *የሚሰማ ሰፊ ጆሮ፥ የሰማውን የሚመረም ትልቅ አእምሮ የነበረው ሰው*
> *መሆኑ ነው። የድርሰቱ ውበት ማንበብ የጀመረ ሳይጨርስ የማይለቀው*
> *ነው። አማርኛዬ የግዕዙን ውበት እንዳስተጋባ ተስፋ አለኝ።*

*ዘርዓ ያዕቆብን "ጆሮና ተመራማሪ አእምሮ" አለው ብለው ከአመኑ "ቴለስኮፕና ካቶሊኮቹ"  ለምን ተጠቀሱ? ለመሆኑ ምን እንዳሉ አውቀዋል? ሲያውቁት የጻፉት "ንጥረ ነገር" ፈላስፋው "አም" ያለዉን ነው፤ "ጆሮ" አካል ፤ ደግሞ "አእምሮ"  ሕሊና መሆናቸዉን ነው። ይህንን አውቀው ቢሆን ኖሮ የጻፉት ይሕ ጸሐፊ በታላቅ ኩራት "ታላቁ ፈላስፋ ጌታቸው ኀይሌ እንዳሉት" እያልኩ ብጽፍ በጣም ደስ ይለኝ ነበር። ይህንን ስል አሁን ታላቅ አይደሉም ለማለት አይደለም፤ ታላቅ ምሑር መሆኖዎን አምናለሁ፤ ዘርዓ ያዕቆብን እንደገና በተረጋጋ መንፈስ ቢመረምሩት ሳያውቁ የጻፉትን አውቀው እንደሚጽፉት እርገጠኛ ነኝ፤ ጽሑፉዎን በችኮላ እንደጻፉት ያስታውቃል፤ ግዲለሽነት ይታይብታል፤ አረፈተ ነገሮች ተዝረክርከዋል፤ የቃላት አገባብ ችግር ጎልተው ይታያሉ፤ አግባብ ያልሆኑ ቃላት ተጠቅመዋል፤ ጽሑፉ ከእርስዎ ችሎታ ጋር አይመጣጠንም። እርስዎ ግዕዙን በተለምዶ በደንብ ያዎቁቷል። የቋንቋ መምሕርም ስለሆኑ የግሱን ዕርባታ ጠንቅቀው ያዉቃሉ፤ ዘርዕ ያዕቆብ የግዕዝ መምሕር ስለሆነ ደግሞም ፍልስፍናዉን የጻፈው በግዕዝ ስለሆነና ትምሕርቱም በልምድ ሳይሆን በወንበር ስለሆነ ከሊላ አካል ሰምቶ ሳይሆን አውቆ የጻፈዉን ፍልስፍና በድጋሚ ቢመለከቱት ሊላ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ ብዮ እገምታለሁ። በመጨረሻ የጻፉትን አርፍተ ነገር ["አማርኛዮ የግዕዙን ዉበት እንዳስታባ ተስፋ አለኝ"] ከአርስዎ ይልቅ ሊላ ጸሐፊ ቢጽፈው ጥሩ ነበር፤ ቀደም ብዮ እንድጻፍኩት "ትርጉሙ በሚገባ ተተርጉሟል" ብያለህ፤ እርስዎ ግን ሲሉት "ዕውነትም ፕሮፌሰሩ ዝና እና ውዳሴ ፈላጌ ናቸው" ብሎ እኔ የሰጠሁትን ትችት ሊደግፍ ይችላል፤ ምን አልባት ማሌቲ ነው። ይህንን ከአልኩ በኃሏ ወደ ሁለተኛው ዘርዓ ያዕቆብ ውይይት አመራለሁ።*

## *2. "የተጻፈ ለተግሳጽና ለትምህርት ተጻፈ"*
## *ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ሰኔ ቀን2 2015 ዓ.ም*

ትእይርቶሙ ለእለ ይትዔየሩከ ወድቀ ላእሌየ። ወኲሉ ዘተጽሕፈ ለተግሳጸ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትእግስትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ" (ሮሜ 15፡ 3) ።

ይህችን ጦማር "የተጻፈ ለተግሳጽና ለትምህርት ተጻፈ" በምትለው ሐረግ ላይ እንድመሰረትታ ያደረገኝ ተጽፎ ከቆየው መጽሐፍ በመፍለቋ ነው። የፈለቀችበት መጽሐፍ ጨካኞች በዜጎቻቸው ላይ መከራ በሚያበዙበት ወቅት መንፈሳቸውን በጽናት በተስፋና በስነ ምግባር እንዲያጠነክሩ የሚያሳስብ ነው። "የተጻፈ ለተግሳጽና ለትምህርት

ተጻፈ” የምትለው ጥቅስ ለዚህች ጦማር ምክንያት የሆነችውን ጥንታዊት ክርታስ አጉልታ ስለምታሳይ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወስድኳት።ይህችን ጥንታዊት ክርታስ ያቀበሉኝ ዶ ክተር ጌታቸው ኃይሌ ናቸው። “የታረዱት ነፍሳት ጩኸት” በሚል ርዕስ ከተባበሩት መንፈሳውያን ህብረት መግለጫ በሚመለከቱበት ወቅት እንዳጋጣሚ ከዚህ በታች የሰፈረችውን ክርታስ የያዘውን መጽሐፍ ይመለከቱ ስለነበር፤ ከተባባሩት መንፈሳውያን ህብረት መግለጫ ጋራ መመሳሰሏ ገርሟቸው ይህችን ክርታስ እንድመለከታት ከመጽሐፉ ቆንጥረው አቀበሉኝ። ክርታሷን ሳነባት፤ በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረውን ዘመን፤ አሁን ካለንበት ዘመን፤ መሪዎችን ከመሪዎች፤ አመራርን ካመራር፤ ጭፍራን ከጭፍራ፤ ካህናትን ከካህናት፤ ክስተቶችን ከክስተቶች ጋራ እያነጻጸረች የምታንጸባርቅ በመሆኗ እጅግ ተገረምኩ። ኢትዮጵያ እኔን ብቻ አልወለደችኝ፤ መገረሙ ለምን በኔ ብቻ ይወሰን፤ በዚህ ዘመን ያለ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ይመለከተታትና እንደኔ ይግረመው ብየ አሰብኩ። ክርታሷ በጥንታዊትነቷ የኢትዮጵያውን ንብረት በመሆኗ ፈቃድ መጠየቅ አስፈላጊ ባይሆንም፤ ከየትና እንዴት ከኔ እንደደረሰች አለመግለጽ የሚያስነቅፍ ነጠቃ ነው። በቅኔ ትምህርት ቤት የሚያስመሰግነው ነጠቃ፤ ባለ ቅኔው ካንደበቱ ሳያወጣው፤ በሚሰጠው ፍንጭ ምሥጢሩን በመቅደም መንጠቅ እንጅ፤  ካንደበቱ ካፈለቀው በኋላ የራስ አስመስሎ መናገር በጥብቅ ክልክል ነው። እንኳን ቅኔ ተራ ነገርም ቢሆን አፍላቂውን ሳይናገሩ ከራስ የፈለቀ አድርጎ ማቅረብ የሰው ሀሳብ ዘራፊ፤ የሀሳብ ሌባ፤ መሳጢ፤ ጥራዝ ነጣቂ （plagiarizer） ተብሎ ከሰውነት በታች ያወርዳል። በቅኔ ትምህርት ቤታችን ስርአት አሥር ሽክም እንጨት ከቆላ ማመላለስን ያስከትላል።

*እጅግ በጣም የሚገርም አርዕስትና ጽሑፍ ነው፤ በመጀመሪያ ከሮሜ 15፡3 የተወሰደው ጥቅስ በግዕዝ “ወኵሉ ዘትጽሕፈ ለተግሳጸ ተጽሕፈ ከመ በተእግስትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንረክብ ተስፋነ” የሚለው  ሐረግ በአማርኛ ግሱ ባለቤት፤ ተሳቤ እና ማሰሪያ ሆኖ ሲተረጎም ስሚት አይሰጥም። ለምሳሌ በቅዳሴ ግዜ “ለይኩን ለይኩን ቡሩክ ለይኩን” የሚለውን ቃለ ዉዳሴ ወደ አማርኛ እንደዚህ ብለው “ይሁን፤ይሁን፤ይመስገን ይሁን” ሲተረጉሙት  ፈጽሞ ስሜት አይሰጥም። ትርጉሙ ቃል በቃል ሳይሆን በአማርኛ ሥዋሰው ደንብ ባለቤቱና ማሰሪያ ግሱ ተቀነባብሮ መጻፍ ይኖርበታል፤ባለቤቱ ማለትም ምስጋና የቀረበው ለክርስቶስ ስለሆነ መባል የነበረበት “ስሙ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን” ነው ስሙ ውስጠ ታዋቂ ስለሆነ። ነገር ገን የግዕዝ ሥዋሰዉ በሚገባ ስለአልዳበረ አረፍተ ነገሮች የሚጻፉት ጸሐፊው እንደመሰለው አድርጎ ነው፤ ከላይ የተሰጠው አርዕስት “የ” ሚለው ቅጽል ቢገደፍ የሚሆነው “ተጻፈ ለተግሳጽና ለትምህርት ተጻፈ” ስለሚሆን ስሚት አይሰጥም ምክናያቱም ግሱ ባለቤትም ማሰሪያም መሆን ስለማይችል፤ ነገር ግን “የ” የሚለው አመልካች ቅጽል ከገባ መጻፍ ያለብት “የተጻፈው ለተግሳጽና ለትምህርት ነው” ተብሎ ነው። የኛ ደብተራዎች  ግዕዙንም ሆነ አማርኛዉን በደንብ አድርገው ስለማያዉቁት የሚጽፉትም ሆነ የሚናገሩት እንደመሰላቸው ነው። አለማወቅ ደፋር ያደርጋል እንደሚባለው ሲያስተምሩም ሆነ ሲገሰጹ በድፍረት ነው። “ሰማይ ትወጣለህ፤ሲኦል ትወርዳለህ እያሉ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሕሊናዉን ከማውገዝ በላይ የሰውን ልጅ በሥነ ምግባር ኮትኩተው ፈሪሐ እግዚአብሔር እንዲኖረው አይደለም። ከላይ የተጠቀሰው አርዕስትና ጽሑፍ የተለመደው ውግዘት ነው። እንደዚህ አይነቱ አባባል ተግሳጽም ትምህርትም አይሆንም።*

*ይህ ከተባለ በኃላ ትልቁ ጥያቄ ለምንድነው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ አንድ ቁራጭ “ክርታስ” ለቀሲስ አስተርአየ ጽጌ እንድሚለኪቷት የላኩት? ክርታሱ የተገኝበት መጽሐፍ ስምና ጸሐፊ ሊኖረው ይገባል፤ ለምንድነው የጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን ያልተገለጸው? በአርዕስቱ ላይ እንደተጻፈው ተግሳጹና ትምህርቱ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ሰራው አረማዊ ተግባር ነው? በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ስለ ዘርዓ ያዕቆብ አረማዊነት የተጻፈ ነገር የለም፤ አሁን ግን አገኙት በተባለው “ክርታስ” አረምዊነቱን ለተግሳጽና ለትምህርት ተብሎ የቀረበበት ለምን ይሆን? ለመሆኑ ፕሮፌሰሩም ሆኑ ቀሲስ አስተርአየ ስለ ዘርዓ ያዕቆብ አስፈላጊዉን ጥናት በማድረግ ነው “አረማዊ ስርአቱን” የተረዳችሁት? ወይስ ደግሞ በተዋህዶ ክርስቲያን ስም የተደራጁ የወያኔ ተለጣፊ “ተሐድሰዎች” ነን በሚሉት ፕሮጋንዳ ተነሳስታችሁ ነው በዘርዓ ያዕቆብ  ላይ የዘመታችሁት? ምክናያቱ ግልጽ አይደለም። ሆኖም አንባቢ ይህንን እውነት ያልሆነ ክስ እንዲመለከተዉና የራሱን አስተያየት እንዲስጥበት ተላከ የትባለዉን “ክርታስ” ግዕዙንና ትርጉሙን በዋቢነት ከዚህ በታች ይቀርባሉ።*

### *“ዶክተር ጌታቸው የላኩልኝ ግእዙ”*
### *ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ*

*ወእምድኅረዝ በፈቃደ እግዚአብሔር ለአከት ኀበ [አቡነ ተክለ ሐዋርያት] ዣን ከለላ ብእሲተ ንጉሥነ ዘርአ ያዕቆብ እሙ ለበእደ ማርያም፤ ወትቤሎ ናዝዘኒ ኀጢአትየ በእንተ ክርስቶስ። ወአሜሃ ሖረ ኀበ ዴዴ ንጉሥ ወናዘዛ ላቲ በከመ ሕግ። ወእምድኅረ ናዘዛ ትቤሎ ንግሥት ለአቡነ ተክለ ሐዋርያት ባእ ኀበ ወልድየ ወባርኮ። ወበእደ ማርያም ለአከ ኀቤሁ ወይቤሎ ባርከኒአ ወናዝዘኒ በእንተ ፍቅረ ክርስቶስ ወበእንተ ፍቅረ ማርያም ወእምዝ ቦአ ኀበ ገላውድዮስ [የበእደ ማርያም ሌላው ስም መሆን አለበት] ወቤተ እንዘ ይምዕዶ ወይናዝዞ በነገረ መጻሕፍት ቅዱሳት።*

*ወእምህየ አብእዎ ኀበ ቤተ ንጉሥ። ወተሰእሎ ንጉሥነ ዘርአ ያዕቆብ ኵሎ ግብሮ ወአፍቀሮ ወአንበሮ ኀበ ዴዴሁ ኀበ ታቦተ ማርያም ድንግል። ወነበረ በህየ ፫ተ አውራኅ። ወበዕለተ በዐለ መስቀል ርእየ አቡነ ተክለ ሐዋርያት በዴዴ ንጉሥ እንዘ ይትዋነዩ ሐራ በአፍራስ እንዘ ይደራበዩ በአእባብ ወበአዕፅምት ወበዘንግ እንዘ ይመውቱ ብዝዙኃን ነፍሳት። ወአንከረ ወይቤ ግዕዘ አረሚኑ ዝንቱ። ወሐዘነ ጥቀ ወይቤ ለምንት እነብር በከ ወኢይጌሥጽ ወኢይሜህር ሕገ። ወእመሂ አበዩኒ ይቅትሉኒ። ወነገሮሙ ለብዙኃን ካህናት ወመነኮሳት 3ይቤሎሙ ለምንት ኢንጌሥጽ ንጉሠ በዘኢኮነ ሕገ። ወይቤልዎን ንሕነሰ ንፈርህ፤ አንተ በል። ወበዕለተ በዐለ መስቀል ርእየ አቡነ ተክለ ሐዋርያት በዴዴ ንጉሥ እንዘ ይትዋነዩ ሐራ በአፍራስ እንዘ ይደራበዩ በአእባብ ወበአዕፅምት ወበዘንግ እንዘ ይመውቱ ብዝዙኃን ነፍሳት። ወአንከረ ወይቤ ግዕዘ አረሚኑ ዝንቱ። ወሐዘነ ጥቀ ወይቤ ለምንት እነብር በከ ወኢይጌሥጽ ወኢይሜህር ሕገ። ወእመሂ አበዩኒ ይቅትሉኒ።ወእምዝ ነበረ እንዘ የሐዝን ሠሉሰ ዕለተ። ወአመ ፳ወ፩ለመስከረም ለአከ ኀበ ንጉሥ ወይቤ ተመጠወኒአ። ብየ ነገር (=ጉዳይ) ኀቤከ። ወይቤሎ ንጉሥ ኢይትከሀለኒ ዮም፤ ወለአከ ኀቤሁ ፩ደ እምሊቀ ደብተራ ዘስሙ ገብረ ኢየሱስ ይንግሮ ሎቱ ነገሮ። ወነገሮ አቡነ (ለውእቱ ደብተራ) ኵሎ ዘይኄሊ ወ(በእንተ) ሞተ ሰብእኒ በከንቱ ወበእንተ ማእሰርት ወዝብጠተ ኮነኔ ዘኢይከውን ዘይትገበር። ወለአከ አቡነ ብዙኀ ነገረ። ወተቃጸቦ ውእቱ ደብተራ ለአቡነ በልሳኑ (= ምላሱን አወጣበት)። ወይቤሎ አብነ ነቢየ አምላክ አንተሂ ኢታመስጥ እምውእቱ መቅሠፍት። ወከማሁ ሞተ ድኅረ በእኩይ ኮነኔ ጽዑር። ወአሜሃ ቦአ (ውእቱ ደብተራ) በመዐት ኀበ ንጉሥ ወአስተዋደዮ ለአቡነ ወይቤ ይጼደቅ (= ይመጻደቃል) ዝመነኮስ ወይዘለፈከ። ወይፀርፍ ብዙኀ ላዕሌከ። ወበእንተዝ ተምዐ ንጉሥ ጥቀ፤ ወአዘዘ ያምጽእዎ ፍጡነ። ወሶቤሃ አብእዎ በጕጕዐ፣ ወይቤሎ ንጉሥ አማንኑ ዘለፍከኒ። መነ ርኢከ እንዘ እቀትል ዘእንበለ ፍትሕ። ወመነ አእመርከ እንዘ እኴንን ወእዘብጥ እንበለ ሕግ፤ ወለምንት ከመዝ ትዘልፈኒ እንዘ መሲሕ አነ። ይቤ አቡነ እንዘ እቀውም ቅድመ ንጉሥ ወረደ ላዕሌየ ኀይል እምአርያሙ ለአምላኪየ፤ ወሰማዕኩ ቃለ ዘይብለኒ ጽናዕ ፍቁርየ። ወእምዝ ተዋሥአ አቡነ ምስለ ንጉሥ ብዙኀ ነገረ በእንተ አንስት ("ማእሰርት" ሳይሆን አይቀርም) ወበእንተ ኮነኔ ወዝብጠት ብዙኀ ወበእንተ ኵሉ ዘኢይከውን ገቢረ። ወበእንተ ድፍረተ ተዋሥኦቱ ተምዐ ንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ ወአዘዘ ይዝብጥዎ አፉሁ ወአእናፊሁ። ወዘበጥዎ ብዙኀ። ወውሕዘ ደም እምአንፉ ወአፉሁ። ወአቡነሂ ተዋሥኦ ወኢፈርሀ ምንተኒ ዝብጠተ። ወነዝሀ ደሞ ውስተ ምድር በቅድመ ንጉሥ፤ ወአጥመቀ በደሙ ሥልሰ ሥዕለ ማርያም ድንግል ምስለ ፍቁር ወልዳ ዘኮነ ይፀውራ በእንግድዐሁ። ወንጉሥኒ ወሰከ መዐተ ሶበ ርእየ ዘንተ። ወዳግመ ዘበጥዎ ብዙኀ። ወአዘዘ ይዕቀብዎ ሐራ ጽኑዓን፤ ወነበረ አቡነ በሕማም። ወካዕበ በኀዳጥ ዘመን ጸውዖ ንጉሥ። ወአሜሃኒ ጸንዐ አቡነ ወተዋሥኦ ለንጉሥ። ወዘበጥዎ ዳግመ በአብትር። ወአዘዘ ንጉሥ ያንብርዎ ውስተ ምንድቅ ምስለ ሐራ።*

## *"የግእዙ ትርጉም"*
## *ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ*

*የንጉሣችን ዘርአ ያዕቆብ ባለቤት፤ የብእደ ማርያም እናት ዣን ከለላ ይባሉ የነበሩት ንግሥት ከዕለታት አንድ ቀን፤ ኃጢአታቸውን ተናዘው ንስሀ ለመግባት ፈለጉና፤ በዘመናቸው የነበሩትን መንፈሳዊ አባት አባ ተክለ ሐዋርያትን ወደ ቤተ መንግሥት አስጠሯቸው። መንፈሳዊው አባትም ጥሪውን ተቀብለው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ። ንግሥቲቱን መከረው አስተምረው ተገቢውን ንስሀ ሰጧቸው። ንግሥቲቱም በእደ ማርያም ይባል የነበረውን ልጃቸውንም እንዲመክሩላቸው እንዲያስተምሩላቸው መንፈሳዊውን አባት ጠየቋቸው። በእደ ማርያምም በእናቱ ምክር ተስማምቶ ከመንፈሳዊው አባት ቡራኬ ለመቀበል ፈቀደ። መንፈሳዊው አባትም መጻሕፍትን እየጠቀሱ በእደ ማርያምን መከረው አጽናንተው ባረኩት። ከዚያ በኋላ መንፈሳዊውን አባት ወደ ንጉሡ አቀረቧቸውና ከንጉሥ ዘርአ ያዕቆ ብ ጋራ ተገናኙ። ንጉሡም የመንፈሳዊውን አባት ብቃትና ችሎታ ለማወቅ ፈልገው፤ ጥያቄዎችን አቅርበውላቸው በሰጧቸው መልስ ብቃታቸውን ከተረዱ በኋላ፤ ከቤተ መንግሥቱ በር አጠገብ በነበረችው በእመቤታችን ስም በተሰየመችው ቤተ ጸሎት (ኒቆታ) ውስጥ እንዲቀመጡ ፈቀዱላቸው። መንፈሳዊው አባትም በቤተ መንግሥቱ ጸሎት ቤት ለሶስት ወራት ቆዩ። በቤተ መንግሥቱ ፊት ለፊት በነበረው ሜዳ ላይ፤ የመስቀል በዓል በየዓመቱ ሲከበር በሚደረገው ስርአት የንጉሡ ጭፍሮች በፈረስ ግልቢያ በመወዳደር እስኪ ጎዳዱና እስኪ ገዳደሉ ድረስ እርስ በርሳቸው በዱላ ባጥንት በዘንግ ሲደባደቡ ሲቀጣቀጡ መንፈሳዊው አባት አዩ ። መንፈሳዊው አባትም፤ ንጉሡ ይህን አረማዊ ባህል ከማረም ይልቅ እንዲካሄድ በመፍቀዳቸው በጣም አዘኑ። መንፈሳዊው አባትም "ይህን ያረመኔ ተግባር እያየሁ በቤተ መንግስት ውስጥ በምቾት በመቀመጥ ጊዜየን በከንቱ ማባከን ነው። ንጉሡን መክሬ አስተምሬ ይህንን አረማዊ ልማድ እንዲያቆሙ መድረግ አለብኝ" ብለው ወሰኑ። በመጀመሪያ በማስቆሙ እንቅስቃሴ ላይ ካህናቱ እንዲተባበሯቸው ጠየቁ። ካህናቱ ግን ከፈለጉ እራሰዎ ያድርጉት እንጅ እኛ ንጉሡን እንፈራለን ብለው ሊተባበሯቸው አልፈለጉም። መንፈሳዊው አባትም፤ ካህናቱ "ባይተባበሩኝም፤ ንጉሡ ምክሬንና ተግሳጼን ባይቀበሉም፤ ሊገድሉኝ ቢፈልጉም ይግደሉኝ እንጅ፤ ይህን አረማዊ ተግባር እያየሁ ዝም ብየ ዘመነኔን በከንቱ አላሳልፈውም" ብለው ወሰኑ። ወደ ንጉሡ ከመቅረባቸው በፊት ለሶስት ቀናት ከአምላካቸው ኃይልና ድፍረት እንዲያገኙ ጾሙ ጸለዩ ። ከሶስት ቀናት ጾምና ጸሎት በኋላ ለግርማዊነተዎ የማቀርበው ትልቅ ጉዳይ አለኝና ይፍቀዱልኝ ብለው መስከረም 21 ቀን ወደ ንጉሡ ላኩ። ንጉሡም ታማኝ አገሊጋዮቻቸው ከነበሩት ከደብተሮች*

አለቆች አንዱ ገብረ ኢየሱስ በሚባለው በኩል “ለዛሬ አይመቸኝም” ብለው መለሱላቸው። መንፈሳዊው አባትም ለንጉሡ ማቅረብ ያሰቡትን ለደብተራ ገብረ ኢየሱስ አካፈሉት። ማቅረብ ያሰቡትም፤ “በቤተ መንግስት አደባባይ ላይ ሰዎች እርስ በርሳቸው እየተደባደቡ እስከ መጋደል መድረሳቸው ለሰው ልጅ ክብር ተስማሚ አይደለም“ የሚል ሲሆን፤ በቤተ መንግሥት በቆዩበት ወቅት የታዘቧቸውን ሌሎችንም ስህተቶች ”መታረም ይገባቸዋል“ ብለው ለደፍተራ ገብረ ኢየሱስ አካፈሉት። ደብተራ ገብረ ኢየሱስ መንፈሳዊው አባት ለንጉሡ እንዲያደርሱላቸው የነገሩትን መልእክት ለንጉሡ ሊያደርስ ይቅርና፤ ራሳቸው ይህን ድፍረት የተሞላ አቀራረብ ለንጉሡ ለማቅረብ በማሰባቸው እጅግ ተገረመ።ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ “ነቢየ አምላክ ሆይ ” ንጉሡ ሠራዊቱ የሚያደርገውን አረማዊ ባህል እንዲያስቆሙ ሊያስደርጉ ይቅርና፤ እርሰዎንስ ከጭፍራው ተቀላቅለው ይደባደቡ ብለው ግርማዊነታቸው ቢያዝዎ ምን ሊሉ ነው ? ብሎ መለሰላቸው። ከዚያ በኋላ ደፍተራው “ ይዘልፍዎታል፤ ይንቅዎታል” እያለ መንፈሳዊውን አባት ከንጉሡ ጋራ የሚያራርቅና የሚያጋጭ፤ የሚያስቆጣ ነገር እየጨመረ ለጉሡ ነገራቸው ። ጉሡም ደፍተራው በነገራቸው የተጋነነ ነገር በመንፈሳዊ አባት ላይ ቁጣቸው ነደደ። “አፍቅሬና አከብሬ በቤተ መንግሥቴ ባስቀምጣቸው እንዴት ይህን ያህል ሊ ንቁኝና ሊደፍሩኝ በቁ ? በፍጥነት አምጧቸው” ብለው ንጉሡ ወታደሮችን አዘዙ። ወታደሮችም መንፈሳዊውን አባት እያዳፉ ወደ ንጉሡ አቀረቧቸው። ንጉሡም “ግርማዊነታችንን እየዘለፉ ለደፍተራው የነገሩት እውነት ነው ? ከህግ ውጭ ማንን ስንገርፍና ስንገድል አዩ ? እንዴት ስማችንን ያጠፉሉ ? ” ብለው በመንፈሳዊው አባት ላይ የቁጣ ቃል አወረዱባቸው። መንፈሳዊ አባትም የንጉሡን ቁጣና ግልምጫ አልተቀበሉም። ይልቁንም “ንጉሥ ሆይ ! ”በቁጣ የተናገሩትን ልሰማዎና ልቀበለዎ ይቅርና፤ የቁጣዎ ቃል ካንደበተዎ በሚጎርፍበት ቅጽበት፤ ከርሰዎ ቁጣ የበለጠ ኃይል ያለው “ወዳጄ ጽና” የሚል ድምጽ ከአምላኬ ዘንድ ሰማሁ“ ብለው በቁጣና በድፍረት ለንጉሡ መለሱላቸው። ቀጠሉና ” ባካባቢዎ የሚፈጸሙት የፍርድ መዛባት፤ ዝሙትና ግርፊያ መቆም ይኖርባቸዋል“ ብለው በድፍረት ተናገሩ።ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብም መንፈሳዊው አባት በድፍረት በመናገራቸው አፋቸውንና አፍንጫውን እንዲደበደቡ አዘዙ። ካፍንጫቸውና ካፋቸው ደም ጎረፈ። ይህ የሚደርስባቸው ሥቃይ ሳይገታቸው መንፈሳዊው አባት ለንጉሡ ሊነገር የሚገባውን ተግሳጽ መናገራቸውን ቀጠሉ። በደረታቸው የነበረችውን የእመቤታችንን ስእለ ኢድህኖ እንደ ውሀ ከሚፈሰው ደማቸው በንጉሡ ፊት ሶስት ጊዜ ቀቡ። ንጉሡም በደማቸው ስእለ ኢድህኖውን ሲቀቡ ባዩ ጊዜ ቁጣቸው እጅግ ነደደ። ድብደባው እንዲቀጥል ትእዛዝ ሰጡ። ወደ ጽኑ እስር ቤትም እንዲወሰዱ ወታደሮችን አዘዙ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ መንፈሳዊውን አባት ከእስር ቤት አስመጧቸው። መንፈሳዊው አባትም ከቀድሞው እጅግ በጠነከረ መንፈስ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን ገሰጿቸው። ንጉሥ ዘርዓ ያእቆብም በመንፈሳዊው አባት ላይ ቁጣቸው የበለጠ ነደደ። አሰደበደቧቸው፤ ወደ ጽኑ እስራትም እንዲመለሱ አዘዙ። የመንፈሳዊ አባት መንፈሳዊ ኃይላቸው እየጋለ ቢሄድም፤ ከበትሩና ከእንግልቱ ጽናት የተነሳ ሰውነታቸው ደከመ ።

ከላይ የተጻፈው የግዕዝና የአማርኛ ትርጉም ስሚት የማይሰጥ ዝርክርክ የአለ ኃሳብ ነው።፡ ሥነ ጽሑፉ የሥዋሱን ደንብ ስለአልተከተለ ምን ለማለት እንደተባለ ለማወቅ ያስቸግራል፤ ለምሳሌ በግዕዙ ላይ “ወ” የሚለው አገኛኝ መስተዋድድና መስተፃምር በቁጥር አምሳ ይደርሳሉ። መስተዋድድ በአራት ነጥብም ሆነ በድርዝ ሰረዝ አይገታም፤ ምክናያቱም ነጠላ ነገሮችን ስለሚያይዝ ። ለምሳሌ “ፀሐየ ወወርኃ ወከዋክብት ወኲሎሙ ሥልጣናተ ሰማይ እለ ይትመየጡ የዓርቡ በመካኒሆሙ ወበአዝማኒሆሙ ወበዓላቲሆሙ ወበአዉርኂሆሙ” የሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተወሰደው ግዕዝ “ወ” የሚለዉን መስተዋድድ በሚገባ አረፈተ ነገሩን አያይዟል፤ እዚህ ላይ አንባቤ በትኩረት ማስተዋል ያለበት “ወ” የሚለው አገናኝ መስተዋድድ በምልክት አልታገደም። ቢታገድ ኖሮ ንባቡ ስሚት አይሰጥም ነበር፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ለቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ያቀበሉት “የዘርአ ያዕቅብ አረማዊነት” የተጻፈበት ግዕዝ ፈጽሞ ስሚት የማይሰጥ ዝርክርክ ያለ አረፈተ ነገር ነው። ማን እንደጻፈው ለግዜው ባይታወቅምም የት እንደተጻፈ ለማወቅ አስቸጋሪ አይሆንም፤ ጽሑፉ “ሃምስ” ስለሚበዛበት የግዕዝ መምህራን ዘይቤው ከየትኛው ክፍለ አገር እንደሆነ ሊነግሩን ስለሚችሉ ጉዳዩን ለባለሚያዎቹ እተዋለሁ። ይህን ከተባለ በኋላ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ስለሰጡት “ሐተታ” እና “ነጸብራቅ” ትንሽ ዉይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው፤ ለውይይቱ እንዲረዳን “ሐተታውን” እና “ነጸብራቁን” ከዚህ በታች ሙሉ በሙሉ ለአንባቢ ይቀርባሉ፤

## “ሐተታ”
## ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

አንባብያን ሆይ ! ይህች ጥንታዊት ክርታስ የያዘችው የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን አረማዊ ስርአት ሲሆን፤ የአባ ወልደ ሐዋርያትን መንፈሳዊ ጽናት፤ የደፍተራ ገብረ ኢየሱስን መሰርይነት፤ የካህናቱን ምንደኛነት እና ሠራዊቱን እርስ በርሱ

*ያጋድል የነበረውን የንጉሥ ዘርአ ያዕቆብን ጨካኝነት አጉልታ ታሳያለች። "አዕይነተ እግዚአብሔር" ነን የሚሉ፤ "ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን" እየተባሉ የሚሰብኩ የሚቀድሱ የሚዘምሩ በዚያ ዘመን የነበሩ ካህናት የሚደረገውን ሁሉ ኃጢአት አስቀድመው በማየት፤ ተባብረው መገሰጽና ማስቆም ነበረባቸው። በእግዚአብሔር አዕይንነታቸው ከሁሉ አስቀድመው የሚደረገውን ግፍ ማየታቸው ይቅርና፤ ያዩት አባት ለማስቆም ተባበሩኝ ቢሏቸው ፈርተው አንተባበርም አሉ። ግን ዝማሬውን ቅዳሴውን ስብከቱን በየደብራቸው ያካሄዳሉ ። እርስ በርሱ የሚያጋድለው የንጉሡ አረመናዊው ተግባርም ጎን ለጎን ይካሄዳል። ከህዝቡ የተሻሉ አዋቂዎች ቅዱሳኖች መስለው እንደ ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ የመሰሉ ሰራዊቱንና ህዝቡን የሚያደነዝዝ፤ ፉከራ መሳይ ስብከታቸውን አላቋረጡም። አረማዊ የሆነውን ባህል እንዲያቆሙ ንጉሡን ከመገሰጽ ይልቅ፤ ህዝቡን ሠራዊቱን ንስሀ ግቡ እያሉ ማደንቆራቸው ሲቀጥሉ ህሊናቸው አልወቀሳቸውም። መንፈሳዊው አባትም "ካህናቱ ባይተባበሩኝም በነ ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ ነገር አቀባባይነት የመጣውን መከራ እቀበላለሁ እንጅ ይህን ያረመኔ ተግባር እያየሁና እየሰማሁ በቤተ መንግስት በምቾት በመቀመጥ ጊዜየን በከንቱ አላባክንም። ንጉሱን መከሬ አስተምሬ ማስቆም አለብኝ" ብለው ወሰኑ። በመጀመሪያ በማስቆሙ እንቅስቃሴ ላይ ካህናቱ እንዲተባበሯቸው ሞከሩ።ወደ ንጉሡ ከመቅረባቸው በፊት ለሶስት ቀናት ከአምላካቸው ኃይልና ድፍረት እንዲያገኙ ጾሙ ጸለዩ ። ይህ ሁሉ ለደብተራ ገብረ ኢየሱስ ሰርግና ምላሽ ነበር። ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ ከመንፈሳዊ አባት የሰማውን ፤ እየገለበጠ ለንጉሡ በማቅረብ ለንጉሡ ተወዳጅነቱን ታማኝነቱን ማረጋገጫ አድርጎ ተጠቀመበት። መንፈሳዊውን አባት ለራሱ የባለሟልነት ማዳበሪያ በማድረግ ለመከራና ሥቃይ ዳረጋቸው። ደፍተራ ገብረ ኢየሱስም፤ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብም፤ ካህናቱም እርስ በርሱ ይጋደል የነበረው ህዝብም በዚህች ዓለም ላይ የሉም። መከራና ሥቃይ የደረሰባቸው አባ ወልደ ሐዋርያትም በዚህች ዓለም የሉም። ለሁሉም ለተሰቃዩ ት ለአባ ወልደ ሐዋርያትትም፤ አባ ወልደ ሐዋርያትን ላሰቃዩ ት ለነ ዘርዓ ያዕቆብም የነበረቻቸው የቆይታ ጊዜያቸው ትንሽ ነበረች። ሁሉም በምታልፈዋ በጥቂት ዘመን ቆይታቸው ሊሚያገኙት ቅንጦትና ድሎታቸው ሲሉ በሰማይና በምድር ለዘላለም ሲያስወቅስና ሲያስከስስ የሚኖር ሥራ ሰርተው አለፉ። አባ ወልደ ሐዋርያት "በተፈጥሮ ሞት የሚመጣውን የአካል መፍረስ ተቀምጦ መጠበቅ ዘመንን በከንቱ ማባከን አሉ" በማይቀረው ተፈጥሯው ሞት ሞተው አካላቸው በመቃብር ከመፍረሱ በፊት፤ በንጉሡ ትእዛዝ በወታደሮች እጅ አካላቸው መፍረሱን መረጡ። የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ሠራዊቶች በተፈጥሮ ሞት መፍረሱ የማይቀረውን የአባ ሐዋርያትን ሥጋ ብትር ቀጥቅጠው በማፍረስ፤ ወደ መቃብር ትልነት ራሳቸውን ለወጡ። አሁን ሁሉም በዚህ ዓለም አጭር ቆይታቸው የሰሩትን ተግባር ተሸክመው በሰማያዊ አምላክ ፊት በዘላለማው ፍርድ ላይ ናቸው። በምድርም በየዘመኑ በሚነሳው ትውልድ እየተወቀሱና እየተከሰሱ ናቸው። አባ ወልደ ሐዋርያት ግን ባጭር ዘመን ቆይታቸው፤ ላጭር ጊዜ በደረሰችባቸው መከራና ስቃይ፤ በዘላለማዊ አምላክ ፊት ዘላለማዊውን ጸጋና ክብር ተቀዳጁበት። በምድርም በየዘመኑ በሚነሳው ትውልድ በምሳሌነታቸው እየተወደሱ እየተሞገሱ ይኖራሉ። አሁንም ለኛ ሕያው መምህራችን ናቸው።*

## *“ነጸብራቅ”*
## *ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ*

*ዘርዓ ያዕቆብ በማይገሰሥ ንጉሣዊ ስልጣናቸው እየታገዙ፤ አረማዊ ስርአታቸውን በመጠቀም፤ በህዝብ ላይ የፈፈጸሙት በደል፤ ዛሬ ራሳቸውን ወደ ንጉሥነት የለወጡ ወያኔዎች በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽሙትን እጅግ የከፋ በደል ያንጸባርቃል። ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ሠራዊታቸውን እርስ በርሱ ያቀጣቅጡ፤ ያደባድቡና ያጋድሉ እንደነበረ። ራሳቸውን ወደ ሞናርኪነት የለወጡ ወያኔዎችም ከህዝቡ አብራክ የፈለቀውን ኢትዮጵያዊ እየመለመሉ እርስ በርሱ በሚያጋድል በቅኝ ግዛት መርኌቸው አሰልጥነው እርስ በርሱ እያጋደሉት ነው። ወያኔዎች ከሰራዊቱ አልፈው፤ ከንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብም በከፋና እጅግ በሰፋ አረማዊ ዘዴያቸው መላ ኢትዮጵያውያን በጎሳና በቋንቋ ከፋፍለው እርስ በርሱ እያደባደቡትና እያጋደሉ ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ሳይቀር ተሀድሶና ማህበረ ቅዱሳን የሚባሉ ድርጅቶ ች ፈጥረው፤ በቀሩት አኀት አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች ላይ በማይታይ ድሮ ባልነበረ ስርአት በነገረ መለኮት እያስመሰሉ ወጣቶችን በመከፋፈል እርስ በርሳቸው እያደባደቧቸው ነው።  ከፕሮፌሰር አስራት ጀምሮ በቅርቡ ቀጥቅጠው የገደሉትን ወጣት ሳሙዔል አወቀን የመሳሰሉ እንደ አባ ወልደ ሐዋርያት መንፈሰ ጠንካሮች፤ እርስ በርስ ኢጋዳይ የሆነውን የወያኔን አረማዊ ልምድ ለማስቆም ተባበሩን ብለው ላካባቢያቸው ካህናት ድምጻቸውን አሰሙ። ካህናቱም ወያኔን እንፈራለን እናንተው ተወጡት ብለው ፊታቸውን ወደ ወያኔ አዞሩ። “ይህን ያረመኔ ተግባር እያየሁ በቤተ መንግስት በምቾት በመቀመጥ ጊዜየን በከንቱ ከማባክን፤ የሚገጥመኝን መከራ መቀበሉን እመርጣለሁ” ብሎ፤ እንደ ሳሙዔል የሚወስን አንድ የሲኖዶስ አባል ወይም አባ የሚባል መነኩሴ ጠፋ። ወያኔ ከሚፈጽመው ተግባር እንዲገታ በማስቆሙ ከመተባበር ይልቅ በተቃራኒው ደፍተራ ገብረ ኢየሱስን ከመሳሰሉት ጋራ በመተባበር የወያኔን አረማዊ ተግባር የሚደግፉ ቆሞሶች ቁጥራቸው በዛ። ወደ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ከመቅረባቸው በፊት ከአምላካቸው ኃይልና ድፍረት እንዲያገኙ ለሶስት ቀናት እንደ ጾሙት እንደ አባ ወልደ ሐዋርያት ወደ አምላክ ከመቅረብ ይልቅ፤ በወያኔ ዘመን ያሉ ሰባቂወች ጳጳሳት ቀሳውስትና መነኩሴዎች ብርታትና ድፍረት ከወያኔ የሚፈልጉ ሆኑ። ወያኔን ከፋፍለህ ኢታግድል ማለት ፖለቲካ መግባት ነው ብለው ዘበቱ። እንደነሱ አባባል የወኔ መመሪያና ተግባር የፖለቲካ ነክኪ የሌለው፤ መገሰጽ የሌለበት፤ ነገረ መለኮት የሚቀበለው ለሰው ልጅ ተስማሚ ነው ማለታቸው ነው። ደፍተራ ገብረ ዮሐንስ ከአባ ወልደ ሐዋርያት የሰማውን መልካም ምክር እየጠመዘዘ ለራሱ ባለሟልነት ማረጋገጫ እያደረገ ለንጉሡ እንዳቀረበው፤ የዘመናችን ሰባቂዎችም ወያኔን ሊመክሩና ሊገሰጹ ይቅርና፤ ለወያኔዎችንም ያልተባለውን ሁሉ ወሬ በማቀበል ወያኔዎችን የከፉ አውሬዎች እየደረጓቸው ነው። በህዝቡ መካከል የሚከሰተውን ሁሉ ወደ ራሳቸው ጥቅምና ዝና እየቀየሩ ህዝቡን ይበዘብዛሉ፤ ከወያኔ ጋራ ያላቸውን ባለሟልነትና ታማኝነት ከፍ ያደርጋሉ። ለወያኔዎች ጨማምረው ወሬ እያቀበሉ እንደ አባ ወልደ ሐዋርያት ያሉትን ያስደበድባሉ፤ ያሳስራሉ፤ ያስገድላሉ። በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበሩት ካህናት፤ ክርስቶስን በመከተል ሐዋርያት የሰሩትን፤ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ እነ ቅዱስ ቄርሎስ ያደረጉትን ለመስራት ከአባ ወልደ ሐዋርያ ጋራ መተባበር ከዘርዓ ያዕቆብ ጋራ ያጋጨናል እያሉ ከአባ ወልደ ሐዋርያት እንደ ሸሹ። አባ ወልደ ሐዋርያትን ብቻቸውን እንዳቆሟቸውም፤ የዘመናችን ቆሞሳት ካህናት ሰባቂዎችም ጠንክረው ለመቆም የሚሞክሩትን አንዳንድ አባቶች ብቻቸውን አቆሟቸው። ህዝቡ የጠንካሮች ካህናትን አቋም አይቶ በምሳሌ በመከተል በነሱ ላይ እንዳይነሳባቸው መናፍቅ ናቸው፤ ማርያምን ከደዋል ብለው አሶሩባቸው። ፖለቲካ ውስጥ መግባት ነው እያሉ፡- አትግደሉ፤ ጉዳም አትድፈሩ፤ አትሰሩ፤ ኢታሳዱ ከሚባልበት አውደ ምህረት ሁሉ ሸሹ። ወደ ማያስከስሰው ዳቦ ድግስ ወደ ሚያበላውና ሳንቲም ለማስለቀም ወደ ሚመቼው ወደ ሽብሸባው ዝማሬውና ቅዳሴውና ስብቀቱ ፊታቸውን አዞሩ። እኩይ ፍልስጣ እንደሚባለው ሰይጣን በነገረ መለኮት እየተቃኙ ለህዝብ ከሚቀርበው ትምህርት፤ ቃላት እየመዘዙ ወደራሳቸው ስሜት ጠምዝዘው ለህዝብ በማቅረብ እጅግ የፈጠኑ ሆኑ። በዚህች ነጸብራቅ “ወደ ሽብሽባ ዝማሬና ቅዳሴ ፊታቸውን አዞሩ” ብየ የተናገርኩትን ወደራሳቸው ፍልስጣዊ ሀሳብ ጠምዝዘው፤ ይኸዋ ያባቶቻችን ስርአት ነቀፈላችሁ ብለው ለየዋሁ ህዝብ ማቅረባቸውን ስለማይተው፤ እኔ ይህን ያልኩበት ቅዳሴው የሚናገረውን በዜማ ሸፍነው መልእክቱን ማፈናቸውን ለመናገር መኑን ለመግለጽ እንጅ፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ሥርአት ለመንቀፍ እንዳልሆነ፤ የደፍተራ ገብረ ኢየሱስ ተማሪዎች ሀሳቤን ከመጠምዘዛቸው በፊት በዚሁ ኢጋጣሚ እንዲገቱ አሳስባቸዋለሁ። በክርስትና ታሪክ እንደ ሐዋርያት በዘመናቸው የነበሩትን አረማውያን፤ ሊቃውንት አበውም በዘመናቸው የነበሩትን ሰባዊ ክብርን የሚያዋርዱ ፤ እንደ አባ ወልደ ሀዋርያት ዘርዓ ያዕቆብን፤ አቡነ ጴጥሮስም ጣሊንን ሲገስጹ እንጅ፤ አሸበሸባችሁ ዘመራችሁ ቀደሳችሁ ድህውን ህዝብ*

*ንስሀ ግቡ አላችሁ በመባል የታሰረ የተገደለ የለም። እንዲያውም ዜጎች በፈጣሪያቸው እየተማረሩ ኢድላችን ነው እያሉ እንደ ወያኔ ያለውን እንዳይቋቋሙ ስለሚያፈዝላቸው ወያኔን የመሰሉ መሪወች ይህን መሳይ የካህናት አቋም ይፈልጉታል። ይደግፉታል ። እነ ማርክስን የፈጠራቸውም ገለልተኛ በመምሰል ከወያኔ አይነቶች ጋራ ሰምና ወርቅ ሆኖ የሚቀርበው የሰባኪዎች （ስብከት） ስብቀት ነው። ስብከትና ስብቀት እርስ በርሳቸው እየተቃረኑ ሀሳብ የሚወራረሱ ቃላት ናቸው። ስብከት ማለት ህዝቡ በጎ ነገር እንዲያስብና እንዲያመነጭ በነገረ መለኮት አቅጣጫ ማሳየት ነው። ስብቀት ግን ህዝቡ እውነቱን እንዳያይ ይልቁንም እርስ በርሱ እንዲከፋፈል። እርስ በርስ መጠራጠርን መፍዘዝን መደንዘዝን እየተናገረ የህዝቡን መንፈስ እንደ ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ በነገረ ሰይጣን መሰበቅ ነው። ስብከት የህዝብን አዕምሮ እየናጠ እምነትን ተስፋን ጽናትን መዋደድድን መግባባትን መደጋገፍን መተባበርን እንዲያመነጭ ማድረግ ነው። ስብቀት ግን ደፍተራ ገብረ ኢየሱስ በዘርዓ ያዕቆ ብና በአባ ወልደ ሐዋርያት ላይ እንዳደረገው፤ ህዝቡን እንደወተት እየገፋ እርስ በርስ መጠራጠርን መራራቅን መጣላትን እንዲያመነጭ ማድረግ ነው። ሁሉም በምታልፈዋ ለጥቂት ዘመን ቆይታቸውና ድሎታቸው ሲሉ በሰማይና በምድር ለዘላለም ሲያስወቅስና ሲያስከስስ የሚኖር ሥራ ሰርተው እንዳለፉ፤ እኛም በትንሿ የቆይታ ዘመናችን በሰማይና በምድር የሚያስወቅስ የሚያስከስስ ህዝብ የሚጎዳ ሥራ እንዳንፈጽምባት እንጠንቀቅ። በተፈጥሮ ሞት የሚመጣውን መፍረስ ተቀምጦ መጠበቅ ዘመንን በከንቱ ማባከን ነው እንዳሉት እንደ አባ ወልደ ሐዋርያት። በህዝቡ ላይ የሚደርሰውን ግፍና መከራ ፖለቲካ ነውና፤ አላይም አልሰማም ምንአገባኝ በማለት የየደብሮቻችን ዘበኞች በመሆን ዘመናችንን በከንቱ እንዳናሳልፈው እንጠንቀቅ። ተወዳጅነትን ታማኝነትን ለማትረፍ ከወያኔዎች ጋራ የቆሙትን ካህናት ከመምሰል ይልቅ፤ በወታደሮች እጅ አካላቸው መፍረሱን የመረጡትን አባ ወልደ ሐዋርያትን እንምሰል። ሁሉም በዚህ ዓለም አጭር ቆይታቸው የሰሩትን ተግባር ተሸክመው በሰማያዊ አምላክ ፊት በዘላለማው ፍርድ ላይ መሆናቸውን አንርሳ። በምድርም በየዘመኑ በሚነሳው ትውልድ እየተወቀሱና እየተከሰሱ መኖራቸውንም አንዘንጋ። አባ ወልደ ሐዋርያት ግን ባጭር ዘመን ቆይታቸው፤ ላጭር ጊዜ በደረሰችባቸው መከራና ስቃይ፤ በዘላለማዊ አምላክ ፊት ዘላለማዊውን ጸጋና ክብር መቀዳጀታቸው አይጠረጠርም። በምድርም በየዘመኑ በሚነሳው ትውልድ በምሳሌነታቸው እየተወደሱ እየተሞገሱ ይኖራሉ። አሁንም ለኛ ሕያው መምህራችን ናቸው። "የተጻፈ ለተግሳጽና ለትምህርት ተጻፈ" እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ ይህች ጥንታዊ ት ክርታስ በዚህ ዘመን ላለን ኢትዮጵያውያን ተግሳጽና ትምህርት መሆኗን እንረዳ ዘንድ እግዚአብሔር ዓይነ ልቡናችንን ይክፈትልን።*

*ከላይ የተጠሰዉን "ሐተታና ነጸብራቅ" ጸሐፊው ከተላከላቸው ክርታስ በላይ ስለ ዘርዓ ያዕቅብ  ታሪክ የሚያቁት ነገር ከአለ ማስረዳትና ማስተማር ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ፤ ነገር ግን መምህሩ የሰጡት "ሐተታና ነጸብራቅ" መሰረቱ ፕሮፌሰሩ በአቀበሏቸው ተረት ከሆን ሃላፊነት የጎደለው ሥራ ስለሆነ ያስጠይቃችዋል። የመምህሩ የግዕዝ ችሎታ እንደ ፕሮፌሰሩ በመስማትና በልማድ ሳይሆን በወንበር ስለሆነ አንድ ዋሾ ደብተራ የጻፈዉን ተረት መሰረተ ቢስ መሆኑን ማወቅ ነበረባቸው፤ ለዚህም ምንም አይነት ምክናያት መስጠት አይችሉም ፤ ለአደረጉት ስሕተት ይቅርታ ጠይቀው  ራሳቸው እንዳሉት "በቅኔ ትምህርት ቤት"ሥራዓት ደንብ መሰረት "የአሰር እንጨት ሸከም ከቆላ" የመሸከም ግዴታ አለባቸው። ምክናያቱን በአጭሩ ማስረዳት አስፈላጌ ነው፤ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ በመግቤያቸው ላይ እንደሚሉት ከሆነ ለአርዕስታቸው የተጠቀሙት ጥቅስ የወሰዱት ከቅዱስ ጳውሎስ መልክት ላይ ነው ይላሉ፤ ቀጥሎም ከፕሮፌሰሩ የተሰጣቸው ክርታስ የመነጨችው ጥንታዊትና ከቆየው መጽሐፍ ላይ በማለት ለአንባብያን ስለ ዘርዓ ያዕቅብ አረማዊነት ሐተታቸዉን ይጀምራሉ፤ ነገር ግን ጥንታዊ የተባለው መጽሐፍ ምን ግዜ እንደተጻፈ ደግሞም ማን እንደጻፈው አያመለክቱም። "በነጸብራቅ" ላይ የአንጸባረቀላቸው ዘርዓ ያዕቆብ "በማይገሰጽ ንጉሣዊ ስልጣኑ የአረማዊነት ሥራዓቱን በመጠቀም በሕዝቡ ላይ የፈጸመው በደል ዛሬ ራሳቸዉን ወደንጉሥነት የለወጡ ወያኔዎች በኢትዮጵያዉያን ላይ የሚፈጽሙትን እጅግ የከፋ በደል ያንጸባርቃል።" እንግዲህ አንባቢ በትኩረት መመልከት ያለበት ዛሬ ወያኔ የሚፈጽመው በደል ከጥንት የአለ ስለሆነ አዲስ ነገር የለም ለማለት ነው፤ ግዕዙም ትርጉሙም የሚለው ይህንን ነው። በምን ዓይነት መለኪያ ወይስ እይታ ነው ይህ "ለተግሳጽና ለትምህርት" የሚሆነው? ከጥንት የነበረው "ሁኔታ" አሁንም አለ ከማለት በስተቀር "ሁኔታዉን" የሚለዉጥ ምን አዲስ ነገር መጣ? መልሱን መመለስ የሚችሉት የጽሑፉ አቀባይና ተቀባይ ስለሆኑ ይህንን ለሁለቱ መምህራን እተዋለሁ። ነገር ግን ስለ ንጉሡ ዘርዓ ያዕቆብ አጭር መግለጫ መስጠት አስፈላጊ ነው።*

*ይህ ጸሐፊ በተወለደበት አካባቤ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በነበረው አፈታሪክ መሰረት ዘርዓ ያዕቆብ የንጉሥ ዳዊት የመጨረሻ 'ልጅ ነው። አፈ ታሪክ ማለት ተረት ማለት ሳይሆን በድርጊት የተደረጉ ነገሮች በቃል የሚተላለፍ ታሪክ ነው። እኛ ኢትዮጵያዉያን የሥነ ጽሑፍ ባህል ስለ አለን እንኳን የንጉሥ ታሪክ የተራ ሰዉም  በጽሑፍ ይቀመጣል። የዘርዓ ያዕቆብም ዘመነ መንግሥት ታሪክ በዓለም ታሪክ ዉስጥ ታዋቂ ቦታ ያለው ነው። ዘርዓ ያዕቆብ*

*በጣም ገኖ የሚታወቀው “ፕሪስተር ጆን” ወይም ደግሞ “የቄስ ንጉሥ” በመባል ነው። አንድ የዉጭ አገር ታሪክ ጸሐፊ እንዳሉት “ዘርዓ ያዕቆብን የሚያህል ስመ ጥሩ ንጉሥ ከኢዛና በኋላ አልነገሰም፤ ከሱም በኋላ የመጡት ከሚኒልክ በስተቀር የሱን ያህል ሊሆኑ አልቻሉም” ይላሉ። ስለ ዘርዓ ያዕቆብ ብዙ የተጻፉ መጻሕፍት አሉ፤ ነገር ግን በሕዝብ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሊላው ትውልድ የተላለፈው የቃል ታሪክ የሚያሳየው ምን ያህል በሕዝብ ዘንድ ታሪካዊ ትዝታ የተወ ታዋቂ ና ተወዳጅ መሆኑን ስለሆነ የማስታዉሰውን ያህል ለአንባቢ አቀርባለሁ። በጽሑፍ ያልተደገፈ ታሪክ የሚል ከአለ አንባቢ ስለ ዘርዓ ያዕቆብ የተጻፉ መጻሕፍትን እየፈለገ ማመሳከር ይችላል። ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ዘርዓ ያዕቆብ የተወለደው በአዋሽ ወንዝ አካባቤ ነው፤ አፉኑም የፈታው በተወለደበት አካባቤ በሚናገሩት በኦሮሞ ቋንቋ ነበር።ገና በሕፃንነቱ እንዳለ እናቱ ንግሥት እግዚ ክብሯ የኑጉሡን ፈቃድ ጠይቃ ዘርዓ ያዕቆብን ወደ ትውልድ አገሯ አክሱም በምትገኘው ደብረ አባይ ገዳም ለትምህርት ላከችው፣ ትግራይ በቅዱስ ቅዳሴ የታወቀ አገር ስለነበር ቅዳሴዉን አጥንቶ በአስር ዓመቱ በድቁና ማገልገሉን ይነገርለታል፤ ከዚያም ወደግሺን ማርያም በመሄድ ትርግሙና ቅኒን አጥንቷል፤ ከዚያም አልፎ አሉ በተባሉት ገዳማት እየተዘዋወረ ጾመ ድጓን አቋቋምን በሚገባ ተምሮአል። ብዙ ወንድሞች ስለነበሩት የመንገሥ እድል አገኛለሁ ብሎ አስቦ ኢያቅም ነበር፤ ስለዚህ እጅግ አድርጎ ያተኮረው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ነበር፤ ለዚህም በዋቢነት ሊቀርቡ የሚችሉት ገና በወጣትነቱ ሳለ የጻፈፋቸው መጽሐፍት ናቸው፤ መጽሐፈ ሚላድ፤መጽሐፈ ብርሃን፤ መጽሐፈ ሥላሴ ናቸው። ከዚህም በላይ እጅግ ያሳሰበው የነበረው የፍትሕ ጉዳይ ነበር፤ የሰው ልጅ የአለአግባብና የአለሕግ ሲጉላላ ሲያይ ሕሊናዉን በጣም ያስቸግረው ስለነበር ፍትሕ የሚያግኝበትን ዘዴ ይፈልግ ነበር፤ ከሁሉም በላይ ካህናቱ በሆነው በአልሆነው ነገር ሲታመሱ ማየቱ እጅግ በጣም ያስቸግረው ነበር፤ ስለዚህም “ሥራዓተ ቤተክርሲቲያን “ የሚል ሕግ በማውጣት ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ ተጉለት በሚገኘው ደብረ ምጥማቅ አማኑኢል በጉባኢ ካህናቱ እንዲስማሙ አድርጓል። ይኸዉም “የሥርዓተ ኦሪት” ተከታዮችና “የሥርዓተ ወንጌል” ተከታዮች በስምምነት ተከባብረው በአንድ መቅደስ ዉስጥ አብረው እንዲቀድሱ አድርጓል። ጽላት “የሥርዓተ ኦሪት” ሕግ ስለነበር ቤተክርስቴያን ያለ ጽላት ልትቆም አትችልም፤ ይህም የሚያመለክተው ጥንታዊ ቤተመቅደሳችን የሙሴ ጽላትን ይዞ መቆየቱን ነው። ዘርዓ ያዕቅብ “ሥራዓት ቤተክርስቲያን” ያለው ዛሬ “ቀኖና” ወይም “ቀነና” የሚሉት ከግሪክ የመጣው ቃል “ካነን” ነው፤ ትርጉሙም ቀጥታ መስመር፤ የማያወላውል መንገድ ማለት ነው፤ ስለዚህ ትርጉሙ በማይገባቸው ቃል ከመጠቀም ይልቅ የሊቀ ሊቃዉንቱን ዘርዓ ያዕቆብን “ሥርዓተ ቤተክርስቲያን” የሚለዉን ቢጠቀሙ የተሻለ ነበር።፡ ይህ የዘርዓ ያዕቆብ መነሻ ታሪኩ ነው።*

*ዘርዓ ያቆብ ማለት የያዕቆብ ዘር ማለት ነው፤ ነገሥታቱ የሚጠሩበት ስም ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ “ይኩኖ አምላክ” ፤ “ሥገወ ቃል”፤ “ወረደ ቃል” ፤ “ልብሰ ቃል” ፤ “ሣህለ ሥላሴ”፤ “ኀይለ መለኮት”፤ “አምነ ሥላሴ” ፤ “በዕደ ማርያም”፤ እያሉ በክርስቴያን ስም ይጠሩ ነበር። ዘርዓ ያዕቆብ ታዋቂ መምህርም ቤሆንም ስለሰው ልጅ ያለው አስተያየት ከራሱ እምነት አብልጦ ነበር። ኦሪትንና ሐዲስን አንድ አድርጎ በመመልከት ተጣምረው እንዲሰሩ አድርጓል፤ ይኸውም የግብፁን ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ሜካኤልንና አቡነ ገበረኤልን አስማምቶ ጥንታዌት ኢትዮጵያ ጥንታዌት ጽላቷን በቤተክርስትያኗ ዉስጥ ይዛ እንድትቆይ አድርጓል፤ የምጥማቅ አማኑኢል ጉባኢ በቂ መረጃ ነው። ዘርዓ ያዕቆብ በሃይማኖት ምክንያት ምላስ አልቆረጠም፤ ካህናቱን በሽምል አልደበደም ፤ ያለምንም ደም አስተምሮ አስማማቷቸዋል። ስለዚህም ነው ቄሱ ንጉሥ፤ ፈላስፋው ንጉስ የተባለበት። ዘርዕ ያዕቅብ በ35 ዓመት እድሚው ሴነግሥ ዘውዱን የጫነው አኩሱም ጽዮን ማርያም ሄዶ ነው። በዘመነ መንግሥቱ ብዙ ችግሮች ገጥመዉታል፤ “ፍትሕ” ለሕብረ ተሰቡ አስፈላጌ መሆኑን ስለተገነዘበ የራሱን ልጅ የሰው ነፍስ ስለ አጠፋ በፍርድ ሸንጎ ቀርቦ ፍርዱን እንዲያጋኝ አድርጓል፤ ምነም እንኳ ካህናቱና መኳንንቱ በልዕሉና በእናት ንግስቲት ስም ሆነው ይቅርታ ቤጠይቁ ዘርዓ ያቆብ ከፍትሕ ጎን በመሆን ፍርድን አልገደፈም። በዚህም ምክናያት በአካባቤው የሚኖሩት ሰዎች ደብረ ብርሃን በሜግኘው መቃብሩ ላይ ፅሐይ ባለሟቋረጥ ብርሃኗን ትሰጣለች እየተባለ የሚነገርለት ስመ ጥሩ ንጉሠ ነገሥት ነው፤ ይህም ፅሐይ በዕውነት ብርሃኗን ትሰጣለች ሳይሆን የሱን ጥሩነት ለመዘከር ታስቦ መሆኑ ግልጽ ነው። ዘርዓ ያዕቆብም ዋና ከተማውን ደብረ ብርሃን ብሎ ያለው የኮሜትን ብርሃን አይቶ እንደሆነ ይነገርለታል፤ ምናልባት ደብረ ብርሃንን የጨረቃ ከተማ የምትባለውን “ጀሪኮንን” ለማድረግ አስቦ ሊሆን ይሆናል፤ ይህም መረጃ የሊለው “ሳይሆን አይቀርም” የተባለ መላ ምት ነው፤*

*ልዕሉ ነፍስ ስለአጠፋ በስቅላት የሞት ፍርዱን ተቀብሏል፤ እናት ነግስቲቱም ከቤተ መንግሥት ወጥታ ገዳም ገብታለች፤ ወደቤተ መንግሥቱም አልመለሰም ስለ አለች ዛሪ ያ ገዳም “እምቤ ለአፄ” እየተባለ ይጠራል። ይህ ለዘርዓ ያዕቆብ ታሪካዌ ስራው መረጃ ነው። በቄሱ ተክለ ሐዋሪያት ስም የተጠቀሰው ታሪክ መነሻው በሥረዕተ ኦሪትና ወንጌል በነበረው ያለመግባባት ነው፤ በእርግጥ ካህኑ ሥርዕት አልባ በመሆን የጉባኢዉን ዉሳኔ አልቀበልም በማለት በእስር ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው አልፏል። ዘርዓ ያዕቆብ በሥርዕት ያምናል፤ ፍትሕ ከሰው ልጅ በላይ ሆኖ ሕግ ከአልሆነ ለሰው ልጅ የሚያመጣው መከራ ብዙ ስለሆነ መከበር አለበት በሎ ስለሚያምን ቤተሰቦቹን እንኳን ከፍትሕ በላይ አድርጎ አልተመለከታቸዉም፤ ፍርድ ሸንጎ ላይ ቀርበው ፍርዳቸዉን እንዲያገኙ አድርጓል።*

*ይህ አልሆነም ከተባለ መረጃ አቅርቦ ዕውነተኛውን ታሪኩን መወያየት ይቻላል። የዘርዓ ያዕቆብ ተቀዳሜ ሚስቱ ንግስት እሌኒ የምትባል የሐድያ መሳፍንት ልጅ ነበረች፤ ከዘርዓ ያዕቆብም በኋላ በዋነኛነት እያማከረች የአገሩን ጸጥታና አንድነት አስጠብቃለች። የዘርዓ ያዕቆብ ታሪክ ከነቤተሰቦቹ የሚያንጸባርቀው ጠቅላላ ኢትዮጵያን ነበር፤ ማለትም ቤተሰቡ ሙሉ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ይወክል እንድነበር ይነገርልታል፤ ለዚህም ነው ታሪኩ "አረማዌ" ነው ተብሎ እንዲጻፍ የተሞከረው።*

*በቤተ መንግሥቱ ፊት ለፊት በነበረው ሜዳ ላይ፤ የመስቀል በዓል በየዓመቱ ሲከበር በሚደረገው ሥርዓት የንጉሡ ጭፍሮች በፈረስ ግልቢያ በመወዳደር እስኪ ጎዳዱና አስኪ ገዳደሉ ድረስ እርስ በራስቸው በዱላ ባጥንት በዘንግ ሲደባደቡ መንፈሳዊ አባት አዩ" በማለት ቀሴስ አስተርአየ የዘርዓ ያዕቆበን "አረማዌነት" ከወያኔ አገዛዝ ጋር እያመሳሰሉ ይጽፋሉ። ይህ ድርጊት ተደርጎም ተሰምትም ስለሚያውቅ "በፈረስ ግልቢያ" ስለ አሉት በአጭሩ ማስረዳት ለአንባቢ ይጠቅማል ብዮ አሰባለሁ፤ "የፈረስ ግልቢያ" ያሉት ምናልባት በዚያ አካባቢ ሥለሚደረገው "ጉግስ" ጨዋታ ይመስላል፤ ታሪኩ እንደዚህ ነው፤ በዚያ አካባቢ ባሕል መሰረት በበዓላት ግዜ ጎልማሳዎች የሚጫወቱት "የፈረስ ጉግስ" ይባላል። በሾላ ሜዳ፤ በቡላ ሜዳ፤ በመሐል ሜዳ፤ ደበረ ብርሃን በሜገኘው በዘርዓ ያዕቅብ ሜዳ በገና፤በጥምቀት፤ታቦት በሜነግስበት ግዜ የሜጫወቱት ጨዋታ ነው። ጨዋታዉም እላይ እንደተባለው ሳይሆን ጎልማሳዎች ፈረስ ላይ ሆነው በዘንግ መከታ እየተመካከቱ ይጫወታሉ፤ ይህም ማለት በፈረስ ላይ ሆነው መከታዉን ሲጫወቱ ዘንጉ ፈረሰኝዉን መንካት የለበትም፤ በሚመካከቱም ግዜ ዘንጉ የወደቀበት ከጨዋታ ዉጭ ይሆናል፤ በስህተትም ዘንጉ ፈረሰኛውን ከነካ መችው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ይህንን ጨዋታ ይህ ጸሐፊ በሕፃንነቱ ግዜ ያየው ስለሆነ ከዚህ የበለጠ መረጃ ይዞ ሊቀርብ አይችልም። ይህ ከተባለ በኋላ እነዜህ ሁለት መምሕራን ለምንድነው ዘርዕ ያዕቅብን ከወያኔ ጋር ማነፃፀር የፈለጉት? ወያኔን አሁን በሜሰራው ስራ ሊተች አይችልም? በምን አይነት ሥራአትና ደንብ የወንበዴዎችና የዘራፊዎች ስራ ከዘርዓ ያዕቆብ ጋር ይወዳደራል? ምኒልክ ጠብቶ ያሳደገዉን የእናቱን ጡት ቆርጧል ተብሎ ጡቱን ሲቆርጥ የሚያሳይ ሐውልት ተሰርቶሎቷል፤ አንድ ስመ ጥሩ ንጉሥ በታሪካችን ዉስጥ ቤገኝ በነፍሰ ገዳይነት ተከሶ ለፍርድ ቀርቧል፤ የወያኔ ስራ ስር ነቀል ነው፤ ከዜህ በፊት ተሰራ የታባለዉን ታሪከ ማጥፋት ዋነኛ ስራው አድርጎ ስለያዘው ዘርዓ ያዕቆብን በእጅ አዙር ማጥፋት ዋና አላማው መሆኑን አንባቢ መገንዘብ ይኖርበታል፤ ወያኔ ዘርዓ ያዕቅብን የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው ብሎ አይቀበልም፤ ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት በፊት ስለአልነበረች የግድ አቀባይና ተቀባይ ፈልጎ ዘርዓ ያዕቆብን ማጥፋት ግዴታ ስለሆነበት ነው "አረማዌነቱ" እንዲጻፍ የተፈለገው ። ከዜህ ሊላ ጽሑፉ የሚያሳየው ነገር የለም፤ ለዚህ ሁሉ መልስ ስድብና ቁጣ ከሚሆን ይልቅ በተረጋጋ መንፈስ አንባቢ ተወያይቶበት ከላይ አንድ ስፍራ ላይ እንደተጠቀሰው "መልካሙ ትውልድ " እንዴመጣ "ሁኔታዎችን" ማመቻቸት ታሪካዊ ግዴታ ነው። ያ መልካም ትውልድ ለመምጣት እንደ አቤል ጭኸት እየጮኸ ነው፤ "ዝመንፈስ ዘመኑ ውእቱ ዘከመዝ ቃሉ ይበጽሕ ሰማይ ወይስኪ" እንደተባለለት።*